
# አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህሩ መምሪያ



## ሶስተኛ (፫ኛ) ክፍል

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የተስማማ

# አማርኛ
# እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ
# የመምህር መምሪያ
# 3ኛ ክፍል

አስማማቶ አዘጋጆች፡-
ትእግስት ዳዊት
ማርቆስ በላቸው
መኮንን ሆርዶፋ

አርታኢ፡-
እንግዳወርቅ እንድርያስ

## ማውጫ


ይዘት ገፅ

መግቢያ ....................v

ምዕራፍ አንድ ጤና ....................1

ምዕራፍ ሁለት ጉርብትና....................15

ምዕራፍ ሶስት. ተረት....................24

ምዕራፍ አራት የጊዜ አጠቃቀም....................37

ምዕራፍ አምስት መጓጓዣ....................48

ምዕራፍ ስድስት ስነ ምግባር....................59

ምዕራፍ ሰባት ግብርና....................71

ምዕራፍ ስምንት ስራ....................85

ምዕራፍ ዘጠኝ ባህል....................98

ምዕራፍ አስር ገበያ....................113

ዋቢ ፅሁፎች ....................126

መግቢያ

ውድ መምህር ተማሪዎች የቋንቋን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባትተማሪዎችን በሚገባ ሊያግዟቸው ይገባል ፡፡

1. ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን... ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው፡፡

2. ለተማሪዎች የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ተማሪዎች መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ እንዲሁም የራሳቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

3. በተማሪ መጽሀፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን እንደየመመሪያቸው በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

4. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ጽሑፍችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዱያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

5. ለተማሪዎች በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የተለያዩ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

## ምዕራፍ አንድ (15 ክፍለ ጊዜ)

## ጤና

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

የጥርስ ንፅህና አጠባበቅ

የምዕራፉ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ባዳመጡት ምንባብ መሰረት የቃል ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- የተሰጣቸውን ምንባብ በትክክለኛው አገላለፅ ያነባሉ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- የአረፍተ ነገር አያያዦችን ለይተው ይጠቀማሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ

መምህር፡-

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ማሰራት የሚያስፈልገው የሚደመጠውን ምንባብ በትኩረት እንዲያዳምጡና የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ነው፡፡

- በመጀመሪያ ቅድመ ማድመጥ ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት ለተማሪዎች ያሰሯቸው፡፡

- የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚቀሰቅስና ከዳራዊ እውቀታቸው ጋር ተዛማጅ የሆኑ የተለያዩ ተግባራትን ሊያሰሯቸው ይችላሉ፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ምንባቡን በጽሑፍ እንዲያገኙት ያመቻቹላቸው፡፡
- በማዳመጥ ሂደት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች በትኩረት እንዲያዳምጡ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን ይጠይቋቸው፡፡

የጥርስ ፅህና አጠባበቅ

አርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አንጃና ኡፋይሴ የሚባሉ የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ኡፋይሴ የጥርስ ንፅህናዋን በመጠበቅ ጎበዝ ስትሆን አንጃ ግን አልፎ አልፎ ነበር ጥርሱን የሚያፀዳው፡፡ ኡፋይሴ አንጃን የጥርስ ንፅህናውን እንዲጠብቅ በተደጋጋሚ ብትመክረውም ሊሰማት አልፈለገም፡፡ ከእለታት በአንድ ቀን አንጃ ጥርሱን በፀና ይታመማል፡፡ ከዚያም ወደ ጤና ጣቢያ ከወላጆቹ ጋር ይሄዳል፡፡

**የአንጃህመም መንስኤ ምን ሊሆን ይችላል?**

ሀኪሙ የህመሙ መንስኤ ጥርሱን በንፅህና አለመያዙ መሆኑን ነግረውት መድሃኒት ሰጡት፡፡ ሃኪሙም ‹‹ከዚህ በኋላ ጠዋትና ማታ ጥርስህን መቦረሽ አለብህ! ካልሆነ ግን ጥርስህ ይነቀላል፤ ለሌላ ህመምም ሊያጋልጥህ ይችላል›› በማለት ያስጠነቅቁታል፡፡ ከዚያም አንጃ ከወላጆቹ ጋር ወደ ቤቱ ከተመለሰ ጀምሮ ጥርሱን በአግባቡ ይቦርሽ ጀመር፡፡ ከጥርስ ህመሙም በቶሎ አገገመ፡፡

ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአዳምጦ

መረዳት ችሎታ ለማሻሻል የቀረቡ ናቸው፡፡

- ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን ሀሳብ በቃላቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በትክክል ማድመጣቸውን በመከታተል በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችም ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በቅጅ/ፍቶኮፒ እንዲያነቡ ይስጧቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፍ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ እንደየትምህርት አቀባበላቸው ለሁሉም ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- በንቃት ለሚሳተፉ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጡ፤ የማይሳተፉ ተማሪዎችን ደግሞ እንዲሳተፉ ያግዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መልሳቸውን ከሰጡ በኋላ ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ ከግበረ መልሱ በመነሳትም ሌሎች ተጨማሪ ተግበራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ካዳመጡት

ምንባብ በመነሳት ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልፁ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ለጥያቄዎቹ ተማሪዎች የተለያዩ መልሶችን በጽሑፍ ማስፈራቸውን ይከታተሏቸው፡፡
- የክፍል ጓደኞቻቸውም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- አይነስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን ፅፈው በቃላቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

- እንደየትምህርት አቀባበላቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡ (ለምሳሌ፡ ቴፕ ሪኮርድርና መቅረፀ ድምፅ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የሚተለለፉ አጫጭር ትረካዎችን በማዳመጥ ፅፈው በመምጣት እንዲለማመዱ ይንገሯቸው፡፡)

ተግባር ሁለት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ. የዚህ ተግባር አላማ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ማሳደግ ሲሆን ለዚህም ይረዳ ዘንድ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ይህን ተግባር በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡

- ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አይነስውራን ተማሪዎች የጥያቄዎቹን መልስ እንዲያነቡ በማድረግ መልሳቸውን ይቀባሏቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንደዬ ትምህርት አቀባበላቸው የትምህርቱን ይዘት በሚረዱበት መልክ ያቅርቡላቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የተቃራኒ ቃላት እውቀት ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው፡

- በቅድሚያ ተግባሩን ሁሉም ተማሪዎች እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡

- በመቀጠልም ሁሉም ተማሪዎች ለቃላቱ ተቃራኒ ፍች መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡ መስማት የሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችላሉ፡፡ አይነስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን የፃፈትን እንዲያነቡ ማድረግ ይችላል፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ምላሾች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች እንዲለማመድ ማድረግ ይችላሉ፡፡

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

*መምህር፡-*

- የዚህ ተግባር ዋና አላማ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ነው፡፡
- በቅድሚያ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተማሪው ማፅሀፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን መመስራታቸውን ያረጋግጡ፤ የመሰረቷቸው አረፍተ ነገሮችም የቋንቋውን ስርዓት የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡላቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስላጊው ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸው፡፡
- አይነስውራን ተማሪዎች በብሬል ከፃፉ በኋላ በቃላቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ ያግዟቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

- ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ እንዲለማመድ ማድረግ ይችላል፡፡

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

የአካባቢና የግል ንፅህና

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡-

መምህር፡-

የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሚዘጋጁት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስና የንባብ ፍላጎታቸውን ከፍ ለማድረግ ነው፡፡

- ተማሪዎች በመፅሃፋቸው ላይ ያለውን ስዕል ተመልክተው ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተው ስለምን ርዕሰ ጉዳይ ሊያነቡ እንደሚችሉ የራሳቸውን ግምት እንዱናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ የመማሪያ መፅሐፍ በብሬል የተዘጋጀ ከሆነ እርሱን እንዲያነቡ ያድርጉ፤ ካልሆነ ምንባቡን በመቅረፀ ድምፅ ያስደምጧቸው፤ ይህም ከልሆነ እርስዎ ወይም ሌላ ተማሪ እንዲያነብላቸው ያድርጉ፡፡
- የምንባብ ተግባሩ በሚከወንበት ወቅት ተማሪዎቹ በፅሞና እያነበቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ከምንባቡ የወጡ የድህረ ምንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- እገዛ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያርጉላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ መልሳቸውንም በቃል ይቀበሏቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙትም የራስዎን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ የተማሪዎቹን የጽሑፍ ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በራሳቸው አገላለፅ በሶስት ዓረፍተ ነገሮች በጽሑፍ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡
- የአካባቢና የግል ንፅህና አንድነትና ልዩነት በጽሑፍ እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን በጽሑፍ ማስፈራቸውን ይከታተሉ፡፡
- ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለፅ የሚቸግራቸው ተማሪዎች ካሉ ተደጋጋሚ ልምምድ የሚደርጉበትን የተለያዩ ስሌችን ይከተሉ፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካለ አስፈሊጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

ሐ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲፅፉ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሩን እንዲያሟሉ ይንገሯቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

መልስ፡-

1. በጤና 2. መድሃኒት 3.ሰዎች

4. የግል ንፅህና 5. የአካባቢውን ንፅህና

ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፡-

- ተማሪዎች ከላይ የቀረበውን ‹‹የአካባቢና የግል ንፅህና›› የሚለውን ምንባብ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- አተገባበሩም ከዚህ ቀደም በተግባር አንድ ላይ በግል አንብበውት የነበረውን አሁን ደግሞ አንድ ጊዜ እርስዎ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ካነበቡልቸው በኋላ ተማሪዎችን በጥንድ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያስነብቧቸው፡፡
- አቀላጥፎ
- ማንበብ፡- አንድን ጽሑፍ በትክክልና በተገቢው ፍጥነት ማንበብና የተነበበውን የማስታወስ ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተገቢው አገላለፅ (ማለትም የዴምፅ ቃናንና ጫናን ለይቶ) ማንበብን ያካትታል፡፡ እርስዎም ተማሪዎቹ የአቀላጥፎ ማንበብ ስሌቶችን ተከትለው ማንበብ መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ተጨማሪ አጫጭር ታሪኮች፣ተረቶች…

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት የተማሪዎችን የተመሳሳይ ፍቺ እውቀት ለማሳደግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ተማሪዎቹ በመፅሀፋቸው ላይ የሰፈሩትን ቃላት ተመሳሳያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ያበረቷቸው፡፡

ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ተገቢው እገዛ ይደረግላቸው፡ አይነስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን በብሬል ካሰፈሩ በኋላ በቃላቸው እንዲያጠኑ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ለተማሪዎች ተገቢውን ግበረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት የጠማሪዎችን የተቃራኒ ቃላት እውቀት ማጎልበት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ ስለተቃራኒ ቃላት ምንነት ለተማሪዎች አስፈላጊውን ማብራሪያ ለክፍል ደረጃቸው በሚመጥን መልኩ ያስረዷቸው፡፡ ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች ለቃላቱ ትክክለኛ ተቃራኒ የሆኑትን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- እገዛ ለሚስያፈልጋቸው ተማሪዎች ተገቢው እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ለሁሉም ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው አስፈላጊው ማበረታቻ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ሐ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአውዳዊ ፍቺ እውቀት ከፍ ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በመጀመሪያ ስለ አውዳዊ ፍቺ ምንነት ለተማሪዎቹ አጭር ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

- በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው እገዛ ይደረግላቸው።
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉና ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጡ።
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ሊሰሯቸው የሚችሏቸው ጥያቄዎችን እንዳስላጊነቱ መስጠትይችላሉ።

መልስ፡-

1. መብላት 2. የተለከፈ 3. ባሰባት 4.አዘውትሮ 5. ብር

መ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ቃላት ተማሪዎች ባለ ሶስትና ባለአራት እግር እያሉ እንዲለዩ የተዘጋጁ ናቸው።

- ተማሪዎች የመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ በሰንጠዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በማስፈር እንዲለዩ ይንገሯቸው።
- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በትክክል መለየታቸውን ይከታተሉ።
- ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው።
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ግብረ መልስ ይስጧቸው።
- ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎች እንዲለማመዱ ያድርጓቸው።

ሠ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት ተማሪዎቹ ነጠላና ብዙ ቁጥር ቃላትን እንዲለዩ የሚያስችሉ ናቸው።

ማስታወሻ

ነጠላ ቁጥር ማለት ነጠላ ውክልና ወይም መጠሪያ ማለት ሲሆን ብዛትን የሚያመለክት ቅጥያዎችን አይወስድም። ብዙ ቁጥር ማለት ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ውክልናዎች ወይም መጠሪያዎች የሚውል ሲሆን ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችንም ይወስዳል።

- ስለነጠላና ብዙ ቁጥር ቃላት የክፍል ደረጃውን በሚመጥን መልኩ ያስረዷቸው፤ ምሳሌዎቹንም ይስሩላቸው።
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄውን የሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
- ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸው።
- ተማሪዎቹ ነጠላና ብዙ ቁጥር የሆኑ ቃላትን መለየታቸውን በተለያዩ መንገዶች ያረጋግጡ።
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ።

መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ሰንጠረዦች፣ ቻርቶች፣ ፍላሽ ካርዶችን…

ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ተግባር አንድ፡- መጻፍ

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት አረፍተ ነገሮች የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው።

- ሁሉም ተማሪዎች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላት በፅሞና በማንበብ አስተካክለው አረፍተ ነገር እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- አረፍተ ነገሮቹን አስተተካክለው በሚፅፉበት ጊዜ የቋንቋውን ስርዓት የተከተለ መሆናቸውና ያረጋግጡ፡፡
- እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ያስተካከሉትን አረፍተ ነገር እየተነሱ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ለመስጠት ይችላሉ፡፡
- በ ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› ላይ የቀረቡትን ተግባራት ተማሪዎች ጠይቀው የመፃፍ ክሂላቸው እንዲዳብር የሚያስችሉ ናቸው፡፡
- ከአንድ ቀን በፊት ትዕዛዙን ይስጧቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጠይቀው ፅፈው መምጣቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በክፍል ውስጥም እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ከተመሪዎች መልስ በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ክፍል አምስት፡- ሰዋሰው

ተግባር አንድ፡- አያያዦች

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎችን አያያዥ ቃላት እንዲለዩ ለማስቻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ ስለ አያያዥ ቃላት ምንነት በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የሰፈረውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- በመቀጠልም አያያዥ ቃላቱንና ሀረጋቱን በትክክል መለየታቸውን ይከታተሉ፡፡

- ተማሪዎቹ እርስ በእርስ በመደጋገፍ የመማር ባህላቸው እንዲዳብር በቡድን (3-5) በማደራጀት እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት ይችላሉ፡፡

ለ. በዚህ ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች አያያዥ ቃላቱን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ቃላቱን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ አረፍተ ነገሮቹን ያዋቅሯቸው አረፍተ ነገሮች የቋንቋውን ስርዓት የተከተሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

**መርጃ መሳሪያዎች፡-** አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን የሚያሳዩ ቻርቶች…

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ስለ ጥርስ ንፅህና አጠባበቅ ጽሑፍ አዳምጠዋል ፡፡ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የቃል ዘገባ አቅርበዋል፡፡ ስለአካበቢና የግል ንፅህና ምንባብ አንብበው በራሳቸው አገላለጽ ጽፈዋል፡፡ ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ አዳዲስ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ በአረፍ ተነገሮች ውስጥ አያያዞችን ለይተው አውጥተዋል፡፡ አያያዞችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችንም መስርተዋል፡፡ በምዕራፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዋናዋና ይዘቶች መነሻ በማድረግም የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች ሰርተዋል፡፡

በአጠቃላይ የምዕራፉ ዋና ዋና አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚከተለትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይገምግሙ፡፡

- ያዳመጡትን ምንባብ መነሻ በማድረግ ዘገባ ማቅረባቸውን በመረጋገጥ፤
- የተሰጣቸውን ምንባብ በትክክለኛው አነባብ ማንበባቸውን በመለየት፤
- ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተክክለኛ ፍቺ መስጠታቸውን በማየት፤
- በአረፍተ ነገሮች ውስጥ አያያዦችን ለይተው ማውጣታቸውን በማረጋገጥ
- ግምገማዎትን ማከናወን ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ፡ሁለት (15 ክፍለ ጊዜ)

### ጉርብትና

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

ጉርብትናና ጠቀሜታው

የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ተመሳሳይ ታሪክ አዳምጠው በድጋሚ ይናገራሉ፡፡
- አጫጭር ምንባቦችን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡ ከጽሑፍ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይፅፋሉ፡፡

መምህር፡-

በዚህ ስር የቀረቡት የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት ከፍ ለማድረግና ዳራዊ እውቀታቸውን ለማነሳሳት ነው፡፡

- በቅድሚያ ተማሪዎችን በተቀመጡበት ቡድን በማደራጀት ስዕሉን ተመልክተው የተረዱትን ሃሳብ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠል ርዕሱን ተመልክተው የሚገምቱትን ሃሳብ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ከዚያም መልካም ጉርብትና ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

## ጉርብትናና ጠቀሜታው

አብሮ መኖር የሰው ልጆችን ማህበራዊ ህይወት ያጠናክራል፡፡ ማህበራዊ ህይወት የሚጎለብተው ደግሞ በሰዎች መካከል መከባበር፣ መቻቻል፣ መረዳዳትና መተማመን ሲኖር ነው፡፡ አቶ አምሃና ወይዘሮ ሃያት በአካባቢያችን የሚኖሩ ጥሩ ጎረቤታሞች ናቸው፡፡ አቶ አምሃ በጎረቤታቸው ሰው ሲታመም የሚጠይቁ፣ የተቸገረን የሚረዱና የተጣላን የሚያስታርቁ በመሆናቸው የሰፈራቸው ሰዎች በጣም ይወዷቸዋል፤ያከብራቸዋል፡፡ ወይዘሮ ሃያትም ቢሆኑ ለሀዘንና ደስታ ደራሽ፣ አመት በዓል ሲመጣ ከራሳቸው አልፈው ለጎረቤቶቻቸው የሚተርፉ፣ በቤታቸው እንግዳ ተቀባይ በመሆናቸው እጅግ የተወደዱና የተከበሩ ሰው ናቸው፡፡

**ከአቶ አምሃና ወይዘሮ ሃያት መልካም ጉርብትና በመነሳት ጎረቤቶቻቸው ለነሱ ምን ያሚያደርጉላቸው ይመስላችኋል?**

ከዚህ መልካም ጉርብትናቸው የተነሳ አቶ አምሃ የመጀመሪያ ሴት ልጃቸውን ሲድሩ ጎረቤቶቻቸው ወደ ቤታቸው በመምጣት የሰርግ ስራውን በመተጋገዝና በመረዳዳት ከዝግጅቱ ጀምሮ እስከፍፃሜው አደመቁት፡፡ እንዲሁም ወይዘሮ ሃያት ሁለተኛው ወንድ ልጃቸውን ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ሲመጣ የምርቃቱን ስርዓት በማድመቅ ከስራው ጀምሮ በእለቱ እስከ ነበረው ስጦታ ድረስ የቀረ አንድም ጎረቤት አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሳ አቶ አምሃና ወይዘሮ ሃያት በጎረቤቶቻቸው ደስተኛ ሆኑ፤ መተማመንንም አተረፉ፡፡ በአጠቃላይ መልካም ጉርብትና ለእርስ በእርስ ማህበራዊ ትስርርና መደጋገፍ ያለው ጠቀሜታ በጣም ብዙ እንደ ሆነ ከላይ በቀረበው ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**መምህር፡-**

**የዚህ ተግባር ዋና ዓላማ ተማሪዎቹ የሚደመጠውን ምንባብ ምን ያህል እንደተረዱት ለመለካት ነው፡፡**

ሀ. ባዳመጡት ምንባብ መሰረት በተማሪው መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድረጓቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በንቃት የሚሳተፉትን በማበረታታ የማይሳተፉትንም እንዲሳተፉ ያግዟቸው፡፡
- በመቀጠል ለመልሶቻቸው ግበረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱ ተነስተው አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዱ ያድረጓቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በጽሑፍ ቀርቦላቸው እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ተለይተው ድግፍ ማድረግዎን እንዳይረሱ፡፡
- ተማሪዎች ምላሽ ከሰጡ በኋላ ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱም ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማለማመድ ይችላሉ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው

- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን እውነት ያልሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ ለምላሾቻቻው ምክንያት እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ይከታተሉ፤ ለመለሱት ምላሽ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሶቻቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡
- የሚሳተፉ ተማሪዎችን ያበረታቱ፤ የማይሳተፉትም እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ትክክለኛ መልስ በመስጠት ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግበረ መልሱ ተነስተው ተጨማሪ መለማመጃ እድል መስጠት ይችላሉ፡፡

**ሐ.በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡**

- ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋግራችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አቅርቡ በማለት ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በጥሩ ሁኔታ ለሰሩ ተማሪዎች ከፍ ያለ ማበረታታት ያድርጉላቸው፤ ሌሎችም እንዲሳተፉ ያደፋፍሯቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች በብሬል ከፃፉ በኋላ ምላሻቸውን በንባብ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ለምላሾቻቸው ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱ ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ.በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ከፍ ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ እንደ አስፈላጊነቱ መስጠት ይችላሉ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የሰሩትን መልስ ይቀበሏቸው፤ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልስ ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን ማሰራት ይችላሉ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተመሪዎች እንደየፍላጎታቸው ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት ዕውቀት ከፍ ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በመጀመሪያ ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ይከታተሉ፤እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ለይነ ስውራን ተማሪዎች የጻፉትን በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ሁሉም ተማሪዎች እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- የድምፅ መቅጃ ቁሳቁሶች፣ ቅንጫቢ ፅሁፎች

ክፍል ሁለት፡- ንባብ ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት››

መምህር፡-

- ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ የቀረበውን ምሳሌ ተመልክተው ምን እንደ ተገነዘቡ ይጠይቋቸው፡፡
- ተማሪዎቹ የራሳቸውን ግምታዊ ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ያበረታቷቸው፡፡
- የምንባቡን ርዕስ ካሁን በፊት ሰምተውት ማወቃቸውን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ለዕለቱትምህርት ያነቃቋቸው፡፡
- ከርዕሱ ተነስተው ምንባቡ ስለምን እንደሚያስረዳ እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡ ምላሽ ለሰጡ ተማሪዎች የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን ይጠቀሙ፡፡
- ምንባቡን እንዲያነቡ ይዘዟቸውና በንቃት ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይመልከቷቸው፡፡ ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ጓደኞቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡላቸው ያስተባብሩ፡፡
- ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን አንቀፅ እንደ ጨረሱ የጊዜ ንባብ ጥያቄውን እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በተማሪው መፅሀፍ በተግባር አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃላቸው መልስ እዲሰጡ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍልጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ምላሻቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡
- የሚሳተፉትን ተማሪዎች በማበረታታት የማይሳተፉትን ደግሞ ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ለሚሰጡት ምላሽ ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱ ተነሳስተው ሌሎች ተጨማሪ ተግባርትን መስጠት ይችላሉ፡፡

**ለ . በዚህ ስር ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዳቸው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል/ሆሄ በመምርጥ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡**

- ተግባሩን በቤት ስራ ወይም በክፍል ስራ መልክ በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን በማረገገጥ የማስታዎሻ ደብተራቸውን በማረም ግብረ መልስ በጽሑፍ ይስጧቸው፡፡
- አይነስውራን ተማሪዎች በጽሑፍ ከሰሩ በኋላ በቃል እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡ እንደየትምህረት አቀባበላቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

**ሐ. በዚህ ተግባር በተማሪው መፅሀፍ ስር በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ወይም ሀረጋት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡**

- ተግባሩን በቤት ስራ ወይም በክፍል ስራ መልክ በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- በመቀጠል ለሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን በማረገገጥ የማስታዎሻ ደብተራቸውን በማረም ግብረ መልስ በጽሑፍ ይስጧቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች በጽሑፍ ከሰሩ በኋላ በቃል እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡

- እንደየትምህረት አቀባበላቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ**

*መምህር፡- ይህ ተግባር የማሪዎችን የአቀላጥፎ ንባብ ከፍ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡*

- ለአቀላጥፎ ንባብ የቀረበውን አጭር ምንባብ አመቺውን ዘዴ መርጠው ያስነብቧቸው፡፡
- በሚያነቡበት ጊዜ ደቂቃ በመያዝ በተባለው ፍጥነት፣ ድምፆችንና ቃላትን በትክክል መጥራታቸውን ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቀው ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ድክመት ያለባቸው ተማሪዎች በተደጋጋሚ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ ፅሁፎች፣ ተረቶች፣ አጫጭር ታሪኮች

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ

*መምህር፡-*

*ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡*

- ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ይመልከቱ፤ በጥሩ ሁኔታ የሰሩትን ተማሪዎች ያበረታቱ፤ ሌሎች ተማሪዎችንም በማበረታታት እንዲሳተፉ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ለቃላቱ ትክክለኛውን ፍቺ ማስቀመጣቸውን ይመልከቱ፡፡ የሁሉንም ተማሪዎች ደብተር ይቃኙ፡፡ እርማትንም ይስጡ፡፡

*ለ.በዚህ ተግባር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የተቃራኒ ቃላት እውቀት ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡*

- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

- አይነ ስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን በብሬል ከፃፉ በኋላ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- የተማሪችን የማስታወሻ ደብተር በማረም ግበረ መልሱን በጽሑፍ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ ተነስተው አስፈላጊ ሆኖ ካገኙ ተጨማሪ ተግባራትን ማሰራት ይችላሉ፡፡

ሐ. በዚህ ተግባር ስር የቀረበው ጥያቄ የተማሪዎችን የውስብስብ ሆሄያት ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተማሪው መጽሐፍ ላይ በቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉትን ውስብስብ ሆሄያት ለይተው እንዲያወጡ ያድርጓቸው፡፡
- በዚህ ተግባር ስር በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ውስብስብ ሆሄያት ከቃላት ውስጥ ለይተው ማውጣታቸውንና እነዚህኑ ሆሄያት ተጠቅመው ቃላትን መመስረታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በተጨማሪም ውስብስብ ሆሄያትን የያዙ ቃላትን በሰንጠረዥ ያቅርቡላቸው፡፡

መ. ይህ ተግባር የተማሪዎችን ቃላት የመመስረት አቅም የሚያጎለብት ይሆናል፡፡

- በተማሪው መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ውስብስብ ሆሄያት በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን መሰራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት የሚከተሉትን መልሶች በግብረ መልስነት መስጠት ይችላሉ፡፡

1.. ጧፍ፣ጧሪ፣ብልጧ

2.ቋንጣ፣ቋንቋ፣ቋቁቻ

3.ትንሿ፣ሻሿ፣ሿሚ

5.ባቷ፣አባቷ፣ልጅቷ

6.ባኗ፣ቃኗ፣የግኗ

መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣ ፍላሽ ካርድ፣ የቃላት ሰንጠረዥ

ክፍል አራት፡- ጽህፈት

*መምህር፡-*

ስለስርዓተ ነጥቦች ምንነትና አገልግሎት የቀረበውን አጭር ማስታወሻ መነሻ በማድረግ የራስዎን ማብራሪያና ምሳሌዎች ይስጧቸው፡፡

- በተጨማሪም የስርዓተ ነጥብ ምልክቶች ለይተው እንዲያውቁ ምልክቶቹን ከስያሜያቸው ጋር ሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ለዚሁ መለማመጃነት በ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› ስር የቀረቡትን ተግባራት ያሰሯቸው፡፡ ስርዓተ ነጥቦችን መለየታቸውንና በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ በተገቢው ቦታ አስገብተው መፃፋቸውን ይመልከቱ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- አስፈላጊውንም ግብረ መልስ ይስጡበት፤ ከግብረ መልሱ ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡-** ስርዓተ ነጥቦችን የያዘ ሰንጠረዥ፣ሻሽ ቦርድ፣ፍላሽ ካርዶች

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች የሚደመጡ ጽሑፎች ቀርበውላቸው አዳምጠው በቃል ተርከዋል፡፡ እንዲሁም ምንባቦችን አቀላጥፈው አንብበዋል፡፡ ለተለያዩ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ ውስብስብ ሆሄያትን ለይተው ቃላትን መስርተውባቸዋል፡፡ የተመረጡ የስርዓተ ነጥብ አይነቶችን ምንነትንና አገልግሎትን ለይተዋል፡፡ ነጠላ ሰረዝ፣ አራት ነጥብ፣ ቃለ አጋኖ፣ ጥያቄ ምልክትና ትዕምርተ ጥቅስን በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪም በምዕራፉ መጨረሻ ላይ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች ሰርተዋል፡፡ መምህር በምዕራፉ መግቢያ ላይ የተቀመጡት ዓላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚከተለትን የምዘና ስልቶችን ይጠቀሙ፡፡

- ያዳመጡትን ምንባብ መልሰው መተረካቸውን በማድርግ፤
- አጫጭር ጽሑፍችን አቀላጥፈው ማንበባቸውን በመለየት፤
- ከፅሁፉ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ መስጠታቸውን በማየት፤
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ማዋቀራቸውን በማየት ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት (15 ክፍለ ጊዜ)

### ተረት

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

የምዕራፉ አላማዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጡትን ተረት ይተርካሉ፡፡
- በተረት ውስጥ ያሉትን ዋና ገፀባህሪያት ይናገራሉ፡፡
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቀው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አጫጭር ተረቶችን ያነባሉ፡፡
- የታሪኩን ዋና ሃሳብ ይፅፋሉ፡፡
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይገምታሉ፡፡
- በተለያዩ ጽሑፎች ውስጥ ያሉ ስሞችን ይለያሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍሰ
- ሰዋስው

**መምህር፡-**

- በእለቱ የሚደመጠውን የምንባብ ወይም የጽሁፍ ርዕስ ያስተዋውቁና ርዕሱን በሚመለከት ተማሪዎቹ ምን እንደሚያስቡ ወይም የሚያውቁት ነገር ካለ እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ተረት ያላቸውን የቀደመ እውቀት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የተማሪዎቹን የማዳመጥ ሂደት አላማ ያለው ማድረግ ይቻል ዘንድ ከምንባቡ ወይም ከሚደመጠው ፅሑፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በሰሌዳ ላይ በማስፈር ወይም ከመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ እንዲያዩ በማድረግ ጥያቄዎችን እንዲያስተውሏቸውና እንዲያጤኗቸው ያድርጉ፡፡
- መልሳቸውንም በቃላቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ለተማሪዎቹ ምንባቡን ሁለት ጊዜ ያህል እንዲያዳምጡት በመንገር የተወሰነ ጊዜ ወስነው በትኩረት እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በፅሑፍ ቀድመው የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቹ፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩ በሚከወንበት ወቅት ተማሪዎቹ ምን ያህል በትኩረት እየተከታተሉ መሆናቸውን ለማወቅ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን ይጠይቋቸው፡፡

ሰማዕቷ እናት

በድሮ ጊዜ አንዲት ፊቷን በእሳት የተቃጠለች እናት ነበረች፡፡ አንድ ከነብሷ በላይ ከምትወደው ልጇ ጋር አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ይች እናት መተኪያ የሌለው ልጇን ለማሳደግና ከእኩዮቹ ጋር እኩል ለማድረግ ደፋ ቀና ስትል ትውላለች፡፡ እናት ጥራ ግራ ያመጣችውን ልጇን ትመግብ ነበር፡፡ ልጇም በአካባቢው ከነበሩት ልጆች ጋር ጓደኝነት መስርቶ አብረው ይጫወቱ ነበር፡፡ ከልጆቹ መካከል አንድ በአካባቢው የተከበረ ልጅ ነበር፡፡ ይህ ልጅ ከባልንጀሮቹ ጋር ለእናቱ አንድ ወደሆነው ልጅ ቤት ሲመጡ አብሯቸው ይመጣል፡፡ ለእናቱ አንድ የሆነው ልጅም ባልንጀሮቹ ወደ ቤቱ ሲመጡ እናቱን አይተው እንዳይንቁት በማሰብ የገዛ እናቱን ‹‹ሰራተኛዬ ናት›› እያለ ያስተዋውቃቸዋል፡፡ ይህንን የሰማችው እናት ግን ቅር አልተሰኘችም፡፡

**የልጁን እናት እሳት ያቃጠላት በምን ምክንያት ይሆን ?**

ከእለታት አንድ ቀን ግን እናት ለልጇ እንዲህ ብላ አወጋችው፡፡ ‹‹ልጄ መልኬ እንዲህ ተጠብሶ የተበላሸው አንተን በእሳት ከተያያዘ ቤት ውስጥ አወጣለሁ ብዬ በመግባቴ ነው፡፡ አንተን በያዝኩት ብርድ ልብስ ጠቅልዬ ከእሳቱ ሳተርፍህ እኔን ግን እሳቱ ክፉኛ አቃጠለኝና በጠባሳ የተበላሸ ፊት ይዤ ቀረሁ›› አለችው፡፡ ልጁም በራሱ ድርጊት ተፀፅቶ ባልንጀሮቹን ሁሉ ሰብስቦ ‹‹ተመልከቱ ይች ሰማዕቷ እናቴ ናት፤የእሷ ውበት ከእኔ ላይ ነው! የእኔ ጠባሳ ደግሞ እሷ ላይ ነው›› በማለት ነገራቸው ይባላል፡፡

ቅድስት ማሪያም ዩኒቨርሲቲ ለስነቃል ማስተማሪያነት ካዘጋጀው ሞጁል ላይ ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ

ተግባር አንድ፡-አዳምጦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥየቄዎች የተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ተማሪዎች ገፀ ባህሪ የሚለውን ቃል ስምተው ላያውቁ ስለሚችል አጭር ገለፃ በመስጠት አስቀድመው ግንዛቤ ያስጨብጧቸው፡፡ ማስታወሻ ገፀባህሪ ማለት በገሀዱ አለም ያሉ ሰዎችን፣ እንስሳት፣ እፅዋትና ሌሎች ነገሮችን ወክለው የሚንቀሳቀሱና በደራሲው የተፈጠሩ የምናብ ሰዎች ወይም ነገሮች ናቸው፡፡
- ጥንድ ጥንድ በመሆን ከምንባቡ የተረደትን ሀሳብ እንዲወያዩበት ያድርጓቸው፡፡
- የተረደንና የደረሱበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ታሪኩን በምን ያህል ደረጃ እንደ ተረዱት የራስዎን ግምገማ ያድርጉ፡፡
- ሁሉምተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተገቢውን ያድርጉላቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ
- ይስጡ፡፡
- አስፈላጊነቱን ካመኑበት ሌሎች ተጨማሪ ተግባትን ይስጧቸውና ተለማምደው በምምጣት ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎችን የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ጥያቄዎቹን ለመስራት ያመች ዘንድ በቅድሚያ ከ 3-5 የሚደርሱ አባላት ያሉት ቡድን ያዋቅሩ፡፡

- ከዚያም ተግባራቱን በቡድን እንዲሰሩ ይዘዟቸው፤ ከቡድኑ አባላት ውስጥ አንድ ተማሪ እንደ ሚያቀርብ ይንገሯቸው፡፡ ይሁን እንጅ አቅራቢው ማን እንደሆነ ቀድመው ይግለፁ፡፡

- በመጨረሻም ከየቡድኑ በየተራ የደረሱበትን ሀሳብ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ግብረ መልስም ይስጡ፡፡ በዚሁ መነሻነትም የተለያዩ ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችም አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምንባብ ወይም ጽሑፍ አዳምጠው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ወይም ለመገምገም የተለያዩ ስሌቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ያዳመጡትን ጽሑፍ በቃል ወይም በጽሑፍ በራስ አባባል እንዲገልፁ በማድረግ፣ ያዳመጡትን በስዕል ወይም በዲያግራም እንዲገልፁ በማድረግ፣ የተጓደለ መረጃዎች እንዲያሟላ በማድረግ፣ ባዳመጡት ጉዳይ ላይ መወያየት መቻላቸውን በማረጋገጥ፣ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን እንዲሰጡ በማድረግ፣ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ ይችላል፡፡

ተግባርሁለት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቃላትና ሀረጋት የተማሪዎችን የቀጥተኛ ፍቺ እውቀት ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር በንግግርም ሆነ በፅሐሁፍ ቃላቱን እንዲጠቀሙባቸው በማድረግ ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ፅሐፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሀት እንዲማሩ መድረግ ይችላሉ፡፡

ይህም ተማሪዎች ቃላትን የመለየየትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታቸው እንዲያጎለብቱ ያግዛቸዋል፡፡ ተማሪዎች ቃላትን ማንበብ ማረም እንኳን የተወሰኑ ቃላትን ብቻ ያውቁና ትርጉም ለመፍጠርና ትርጉም ያለው ነገር ለመፍጠር ይቸገራሉ፡፡ ስለዚህ ቃላትን በተለያዬ አይነት መንገድ መማራቸው ጠቃሚ ስለሆነ የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

- ተማሪዎች አውድን ተጠቅመው ለቃላት ትርጉም በመስጠት የተማሯቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቅመው አንቀፅ መፃፍ ይችላል፡፡ (ይህም የሚያነቡትን

እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡ ሀሳባቸውን ግልፅ በሆነ መንገድ እንዲያስተላልፉ ያስችላቸዋል፡፡ ቃላትን ከጽሑፍ ውስጥ ለይቶ በማውጣት መጠቀም ስለሚያስችላቸው በተለያየ ስሌት ቃላትን እንዲማሩ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡)

- በመጨረሻም ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላት ቀርበዋል፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ለቃላት ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደግላቸው፡፡

መልስ፡-

1. ነገረችው 2. መስዋዕት የሆነችዋ 3. ሽፍኜ 4 ደክማ
5. ለፍታ 6. አቻ የማይገኝለት፣ አንዴ ብቻ የሚገኝ

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ እንዲለማመዱ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ለተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎች ያዘጋጁትን መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ከመልሳቸው በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- እንዳስፈላጊነቱም ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ማድረግ ይችላሉ፡፡

መልስ፡-

1. መተው 2. መልከ ጥፉ 3.ተንደላቀቅኩ፣ ተመቸኝ
4. ምንም ጠባሳ የለብኝም 5. መደሰት

ሐ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የተመሳሳይ ቃላት እውቀት ለማሻሻልና የጽሑፍ ክሂላቸውን ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ በመፅሀፋቸው ላይ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ በመቀጠል ባገኙት ፍቺ አረፍ ተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

- የመሰረቱት አረፍተ ነገር የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ መሆኑን ክትትል ያድርጉ፡፡
- ካላይ ለቀረቡት ተግባራት ምዘናዎችን ይስጡ፡፡
- ከምዘናው በመነሳት ተጨማሪ ተግባራት የሚያስፈልጉ ከሆነ ተማሪዎቹ እንዲሰሩ ያድርጉ፡
- ፈጣን፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ያማከሉ የማስተማሪያ ስልት ይከተሉ፡፡ (ለምሳሌ፡- ለፈጣን ተማሪዎች ከበድ በሚል ቃላት እንዲሰሩ ያድርጉ፤ ዝቅተኛ ችሎታ ላላቸው ቢያንስ መፅሀፋቸው ላይ የቀረቡ ተግባራትን በአጥጋቢ ሁኔታ መስራታቸውን ያረጋግጡ፤ በመጨረሻም አስፈሊጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ የመለማመጃ ተግባራት ይስጧቸው፡፡)

መልስ፡-

1. አረረ፣ 2.ተበከለ፣ቆሸሸ 3.ሳድንህ፣ ስታደግህ

4 የተወደሰ፣የተመሰገነ 5.መቆጨት

1. የተጋገረው ቂጣ አረረ፡፡
2. ውሃው ተበከለ፡፡
3. ከጥፋት የሚያድንህ ስራህ ነው፡፡
4. ጎበዝ ተማሪ በመምህሩ የተወደሰ ነው፡፡
5. ባህልህ ሲጠፋ መቆጨት ተገቢ ነው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ካርድች፣ የተለያዩ ተረቶች፣ ሻሽቦርድ…መጠቀም ይችላሉ፡፡

ክፍል ሁለት፡- ንግግር

ተግባር አንድ፡- እንቆቅልሽ

መምህር፡-

ሀ. ይህ ተግባር የሚያገለግለው የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር ነው፡፡

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ተማሪዎቹን አራት አባላት ባለ ቡድን ያደራጇቸው፡፡ ቡድኑን ሲመሰርቱ የፆታ ስብጥሩን የጠበቀ እንዲሆን ያደርጉ፡፡
- ተማሪዎች በፍላጎታቸው የእንቆቅልሹ ጠያቂና መላሽ እንዲሆኑ እድሉን ይስጧቸው፡፡
- የእንቆቅልሽ አጠያየቅ ሂደቱን ጠብቀው እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡
- የጠያቂና የመላሽ ሂደቱን ተማሪዎች በሚያውቁት መንገድ እንዲከተሉ ይንገሯቸው፡፡
- በተጨማሪም ተማሪዎቹ እርስ በእርስ በነፃነት የመናገር ልምዳቸው እንዲዳብር ሌሎች የጭውውት ተግባራትን ይስጧቸው፡፡ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡

መልስ፡-

1. ባህር 2. እሳት 3. ጀበናና ሲኒ 4. ሰዓት
5. ወፍጮ

ክፍል ሶስት፡- ንባብ

ዛፎች

መምህር፡-

- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስዕሉን ተመልክተው የተገነዘቡትን ሃሳብ ይቀበላቸው፡፡
- ከዳራዊ እውቀታቸው በመነሳት ዛፍችን የተመለከተ ሀሳብ እንዲናገሩ በማድረግ የንባብ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡
- ንባቡን ለማንበብ እገዛ የሚሹ ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያመቻቹ፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ምንባቡን የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ፡፡ የንባብሂደቱ በሚከወንበት ወቅት የንባብ ጊዜ ጥያቄውን እንዲመልሱ ይንገሯቸው፡፡

**ተግባር አንድ፡ አንብቦ መረዳት፡-**

*መምህር፡-*

*ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡*

- *ከምንበባቡ የተረደትን ሀሳብ ጠቅለል አድርገው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡*
- *ተማሪዎች ተረቱን አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን በቃል መልስ እዱሰጡበት ያበረታቷቸው፡፡*
- *እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈሊጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡ የተሻለ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ተማሪዎች ማበረታቻ ይደግላቸው፡፡ በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ለማዳበር ታስቦ ተዘጋጁ ናቸው፡፡*
- *ተማሪዎቹ በተረቱ ውስጥ  የቀረቡትን ገፀባህሪያት መለየታቸውንና ማንን ወክለው እንዲቀርቡ መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡*
- *የተረቱን ፊሬ ሀሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡ መስራታቸውንም ክትትል ያድርጉ፡፡*
- *ግብረ መልስ ይስጡ፡፡ በዚሁም መነሻነት እንዲስፈላጊነቱ ተጨማሪ መልመጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡*
- *ለዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው አካታች የማስተማሪያ ዘዴን ይከተሉ፤ግብዓትም እንዲያገኙ ያግዟቸው፡፡*
- *ልዩ ልዩ የምዘና ስልቶችን ይከተሉ፤የትምህርቱ አላማ መሳካቱንም ያረጋግጡ፡፡*

*ተግባር ሁለት፡- ቃላት*

*መምህር፡-*

*በዚሁ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት የሚያሳድጉ ናቸው፡፡*

- *በቅድሚያ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ስለአውዳዊ ፍቺ ምንነት የክፍል ደረጃቸውንና እድሜያቸውን ያገናዘበ ማስታወሻ ወይም ገለፃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡*

- ይህ የቃላት ትርጉም ለማስተማር ጠቃሚ መንገድ በመሆኑ በልዩ ትኩረት እንዲሰሩ ቢያደርጉ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ማጎልበት ይቻላል፡፡
- በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ ባሉ ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውደዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድረጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ልዩ ለሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ድጋፍ አይለያቸው፡፡

ተግባር ሶስት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፡-

- ከዚህ ቀደም ስለ አቀላጥፎ ማንበብ አተገባበርና ምንነት በምዕራፍ ሁለት ላይ የተቀመጠውን ማስታወሻ ያስታውሱ፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ አቀላጥፎ ማንበብ ሊዳብር የሚችለው በርካታ ልምምድን ከተገቢ ግብረ-መልስ ጋር በመስጠት ስለሆነ ተገቢውን ትኩረት ይሰጡ፡፡
- ስሆነም ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቀው የተሟላ ፍቺ ማስተላለፍ በሚችል መልኩ ‹‹ጭልፊቷ›› የሚለውን ተረት አቀላጥፈው ማንበባቸውን ይከታታሉ፡፡
- አቀላጥፈው ማንበብ የሚያቅታቸውን ተማሪዎች በተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፤ የተሻለ አቀላጥፈው የማንበብ ችሎታ ያላቸውን የቃል ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- በተጨማሪም የተለያዩ የአቀላጥፎ ማስተማሪያ ስልቶችን እንደ ጥንድ ንባብ፣ የህብረት ንባብ፣ ማሚቶ ንባብ… እንደ ክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ይጠቀሙ፡፡

ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ተግባር አንድ፡- መፃፍ

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል የሚያዳብሩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

- በተማሪዎች መፅሀፋ ላይ ላይ የሰፈሩትን ቃላት አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱባቸው ያድርጉ፡፡
- እገዛ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትንም እንደ አስፈላጊነቱ ያሰሯቸው፡፡

ለ. የተማሪዎችን የንባብና የጽሑፍ ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

- ተማሪዎች የተለያዩ የተረት መፅሀፍ ትንፈገው እንዱያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ካነበቧቸውተረቶች ተነስተው የወደዱትን ተረት ፅፈው ክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ የድርጉ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎቹን እንደዬትምህርት አቀባበላቸው በሶስት በመመደብ ፍላጎታቸውን ያማከለ እገዛ ይስጧቸው፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ሀሳባቸውን በብሬል ከጻፉ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ልዩ ልዩ የተረት መፅሀፍትን አንብበው በአጫጭር አረፍተ ነገሮች መልዕክቱ እንዲገልጹ በማድረግ ክሂሉን ይበልጥ የመለማመድ እድልን መፍጠር ይችላል፡፡ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን በመጠቀም ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ በዚሁ መነሻነት ክሂሉን ሊያዳብሩ የሚችል ልዩ ልዩ መልመጃዎችን በመስጠት እንዲለማመድ ያድርጉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ስሞችን መለየት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር የሚቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎች ስሞችን እንዲለዩዩ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- የተሰጡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ስሞችን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ልዩ ድጋፍ ሚስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- በተማሪዎቹ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ሰንጠረዥ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የስም ምድቦችን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- በአጠቃላይ የስምምነትን በክፍል ደረጃቸው መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተለያዩ ተጨማሪ ስሞችን ከአረፍተ ነገር ላይ ለይተው እንዲያወጡ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን መስጠት ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎች የራሳቸውን አረፍተ ነገር ከመሰረቱ በኋላ በመሰረቱት አረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ስሞችን እንዲለዩ በማድረግ አማራጭ የመለማመጃ ዘዴዎችን መከተል ይችላሉ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች ድጋፍዎት አይለያቸው፡፡ እንደዬፍላጎታቸው የተለያዩ ተግባርትን ይስጧቸው፡፡
- የተለያዩ የምዘና ስልቶችን በመጠቀም ስሞችን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ከዚሁ ግብረ መልስ በመነሳት ተጨማሪ ማጠናከሪዎችን ይስጧቸው፡፡

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ካዳመጥናቸውና ካነበብናቸው ተግባራት በመነሳት የተለያዩ ተረቶችን ተርከናል፤ እንዲሁም ፅፈናል። በተረቱ ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች ለይተናል። ከዚህም በተጨማሪ አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፈን አንብበናል። ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቀን ድምፃችንን ከፍ አድርገን ተረቶችን አንብበናል። ከምንባቦች በመነሳት የታሪኩን ዋና ሀሳብ ፅፈናል። ለአዳዲስ ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ሰጥተናል። በሰዋስው ክፍል የስሞችን ምንነት ለይተናል። በምዕራፍ ዋና ይዘቶች አማከኝነት ለተዘጋጁት የክለሳ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጥተናል።

በአጠቃላይ በምዕራፉ መግቢያ ላይ የሰፈሩት አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን በተለያዩ የምዘና ስልቶች መለካት ይቻላል።

- ከነዚህም ውስጥ ለተማሪዎች ተረት በመንገር ደግመው እንዲተርኩ ማድረግ፣
- ካዳመጡት ተረት በመነሳት የዋናውን ባለታሪክ ማንነት በመጠየቅና እንዲናገሩ በመድረግ፤ አጭ ርተረት በማዘጋጀት ድምፅዎን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ
  እንዱሁም በልዩ ልዩ ፅሁፎች ውስጥ ያሉ ስሞችን እንዲለዩ በማድረግ መለካት ይቻላል።

# ምዕራፍ አራት (15 ክፍለ ጊዜ)

## የጊዜ አጠቃቀም

**ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር**

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

***መምህር፡-***

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለሰዓት አጠቃቀም አዳምጠው ይወያያሉ፡፡
- ፅሑፉን አንብበው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡
- በቃል እየተነገራቸው አረፍተ ነገሮችን ይፅፋሉ፡፡
- የተውሶ ቃላትን ይለያሉ፡፡
- ግሶችን ይለያሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

- ተማሪዎች ስለጊዜ አጠቃቀም ያላቸውን የቀደመ እውቀት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የማዳመጥ ፍላጎታቸውን የሚያነቃቃ ስልትና ዘዴ ይጠቀሙ፡፡
- አተገባበሩም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ፅሐፍ ሲያነቡ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የማዳመጥ ተግባሩን ይከውናሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በአንድ ጊዜ ነው፡

- ለተማሪዎቹ ምንባቡን ስንት ጊዜ ያህል እንደሚያዳምጡት በመንገር የተወሰነ ጊዜ መድቦ በትኩረት እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡
- ካዳመጡ በኋላ ተማሪዎቹ በቡድን ሆነው እየተወያዩ ለአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቱ፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ምንባቡን በፅሑፍ ቀድመው የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቹ፡፡
- ተማሪዎች እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**‹‹የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች››**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ሁሉም ሠላም ነው? ትምህርታችሁን በአግባቡ እየተከታተላችሁ ነው? ልጆች የነገ ሀገር ተረካቢዎች መሆናችሁን ታውቃላችሁ አይደል? ተረካቢዎቹ እናንተ ስለሆነናችሁ በርትታችሁ መማር አለባችሁ፡፡ ወላጆቻችሁና መምህሮቻችሁ በጥሩ ሥነ ምግባር ታንፃችሁ እንድታድጉ ይጥራሉ፡፡ እናንተም ደግሞ ጥሩ ተማሪዎች ሆናችሁ የተለያዩ የሕይወት ክሂሎቶችን መቅሰም ይኖርባችኋል፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ለመልካም ስብዕና መሠረት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ለትምህርት ጠንካራ ፍላጎት ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ በተቻላችሁ መጠን የተለያዩ መንገዶችን እየፈጠራችሁ ማንበብ፣ መፃፍና ትምህርትን መውደድ አለባችሁ፡፡ የጥናትንም ጥቅም ካወቃችሁ መልካም የአጠናን ዘዴን መከተል ለላቀ ውጤት ያበቃችኋል፡፡ በዘመናዊና ሣይንሳዊ የአጠናን ዘዴ ዋናው ጉዳይ የጊዜ አጠቃቀም ነው፡ ፡ ስለዚህ በአንድ ቀን ውስጥ ያሉትን ሃያ አራት ሰዓታት በሚገባ ከፋፍሎ መጠቀም ውጤታማ ያደርጋችኋል፡፡

**ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምን ተረዳችሁ ?**

ስለሆነም ከወላጆቻችሁ ጋር በመተጋገዝ የጊዜ አጠቃቀም ሠሌዳ ለማዘጋጀት ጥረት አድርጉ፡፡ የጥናት ሠሌዳውን ስታዘጋጁም አጥኚዎች ለጥናት የሚገ|ገለባቸውን ቁሶችና ንቁ የሚሆኑባቸው ሰዓታት በምሣሌነት በመውሰድ መምረጥና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በተቻለ መጠን ለጥናት የሚመች ቦታ መርጦ ለመጠቀም መሞከር ለጥሩ ውጤት ያበቃልና ችላ አትበሉ፡፡ ልጆች ሀገራችን ለነገ ትልልቅ መሪዎች፣ ሣይንቲስቶች፣

ሐኪሞች፣ ግንበኞች፣ በአጠቃላይ በሁሉም የሙያ ዘርፎች የላቀ ሙያ ባለቤት የሆኑ ትውልድ አባላት ያስፈልጓታል፡፡ ስለዚህም እናንተ ልጆች፣ የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች ቁልፉ ትምህርት መሆኑን ተረድታችሁ ጊዜያችሁን በመጠቀም በመማር፣ በመጠየቅና በመመራመር ብቁ ትውልድ እንድትሆኑ ያስፈልጋል፡፡
አስመረት ብስራት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት 15/2013 ዓ. ም ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**መምህር**

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ቀደም ሲል የተሰጣቸውን ጽሑፍ አንብበው ምላሻቸውን በፅሑፍ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- የተማሪዎቹን የትምህርት አቀባበል መሰረት ያደረጉ ተጨማሪ ተግባራትን ቀድመው በማዘጋጀት ሊሰጧቸው ይችላሉ፡፡
- ለሚሳተፉ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጡ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ተግባራቱን የሚሰሩበትን መንገድ ያመቻቹ፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**መምህር፡-**

በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ቃላትን በተለያየ አይነት መንገድ መማራቸው ጠቃሚ ስለሆነ ነው፡፡

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ እንዲያዛምዱ ቀርቧል፡፡
- ይህንንም ተግባር ተማሪዎቹ መስራታቸውንና ለቀረቡት ቃላት ትክክለኛ ፍች መስጠታቸውን እርስዎ በመረጡት መንገድ እርማት ይስጡበት፡፡
- ግብረ መልስ በሚያስፈልግበት ጊዜም አስፈላጊውን ምላሽ ይስጡ፡፡

- ለቃላት ፍቺ ለመስጠት የሚቸገሩ ተማሪዎች ካሉ በመለየት ቀለል ያለ ቃላትን በመስጠት እንዲለማመዱና ቃላትን በንግግርና በፅህፈት ውስጥ እንዲጠቀሙ ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡

መልስ፡- 1. ለ　　2. ሐ　　3. ሀ　　4. ረ

5. ሰ　　6. ሠ　　7. መ

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

**መምህር፡-**

**በ‹‹ሀ›› እና በ‹‹ለ›› ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማሻሻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡**

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የአረፍተ ነገሩን አወቃቅር ይመልከቱ፡፡
- የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀማቸውን ያስተውሉ፡፡
- አቅማቸውን መሰረት ያደረገ የቃላት አጠቃቀማቸውን ይከታተሉ፡፡
- በመጨረሻም ሰፊ ክፍተት አለ በሚሉበት ቦታ ላይ ግብረ መልስ ይስጡ፤ ግብረ መልሱን መነሻ በማድረግ ተጨማሪ ተግባራትን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ የሆነ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎቹን እንደየ ትምህርት አቀባበላቸው የተለያዩ ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡
- ይህ ተግባር ፅህፈትን ለማስተማር እንደመዘጋጀቱ መጠን ተማሪዎች ነፃ ሆነው መፃፍን እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተማሪ መፅሀፍ ላይ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣ የሚነበቡ አጫጭር ታሪኮች**

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

### ተግባር አንድ፡- ምልልስ

***መምህር፡-***

***ሀ. ይህ ተግባር መሰረቱ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ሲሆን አቀራረቡም በምልልስ መልክ ነው፡፡***

- ስለዚህ ተማሪዎች መጀመሪያ ቀደም ብለው በጥንድ ካደራጇቸው በኋላ ስለጎበኟቸው ቦታዎች እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ከዚያም በክፍል ውስጥ ያጠኑትን በጥንድ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

  **ምሳሌ**፡- ተማሪ 1 ፡- ምን ያስደትሃል?

  ተማሪ 2 ፡- መዝናኛ ስፍራ መሄድ፡፡

  ተማሪ 1 ፡- የወደድው የትኛውን መዝናኛ ነው?

  ተማሪ 2 ፡- አንበሳ ግቢ፡፡ አንችስ?
- በዚህ መልኩ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ምልልስ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትንም ሊያሰሩ ይችላሉ፡፡
- ይህ ተግባር የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከማሳደጉ በተጨማሪ ስርዓት ጠብቆ በተራ መናገርን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

***መምህር፡-***

- የቀደመ እውቃተቸውን ለመቀስቀስ የሚያስችለ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ሰፍሯል፡፡
- ስለሆነም ከጊዜ አጠቃቀም ጋር ያላቸውን ልምድ እንዲናገሩ፤ ልምድ እንዲለዋወጡ በማድረግ፤
- በመጨረሻም የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በመስራት ዳራዊ እውቀታቸውን መቀስቀስ ይችላሉ፡፡
- የምንባቡን ሀሳብ እንዲገምቱ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትንም ሊያሰሯቸው ይችላሉ፡፡

- ለንባብ የተመደበውን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በማንበብ ሂደቱ የንባብ የጊዜ ንባብ ጥያቄውን እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

***መምህር፡-***

***ሀ. በዚህ ትግበር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡***

- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መልሳቸውን በቃል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

***ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማዳበር የሚያግዙ ናቸው፡፡***

- በዚህ ክፍል ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው በጽሑፍ እንዲመልሱ ያግዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው እንክብካቤ ይደረግላቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

***በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት አውዳዊ ፍቺ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የተዘጋጁ ናቸው፡፡***

- ሁሉም ተማሪዎች በሰንጠረዡ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲፅፈ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን እንዲናገሩ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጓቸው፡፡
- የተለያዩ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ምዘናዎችን ይጠቀሙ፡፡
- ምዘናውን መሰረት በማድረግ አስፈልገውን ግብረ መልስና ተጨማሪ ተግባራት ይስጡ፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛ ይደረግላቸው፡፡

- እንደተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ልዩ ልዩ ተግባራትን በመስጠት ሰፋ ያለ ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡
- አስፈሊጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች የቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

መልስ፡- 1.ጢም ብሎ 2.መምህር 3.ስራ 4.ጥቃቅን 5.ጥቅም 6.ትኩረት

**መርጃ መሳሪያ፡- ቅንጫቢ ጽሑፍች፣ አጫጭር ተረቶች፣ ሻሸ ቦርድ**

**ክፍል አራት፡- ቃላት**

**ተግባር አንድ፡- የተውሶ ቃላት**

**መምህር፡-**

| **ማስታወሻ** |
|---|
| የተውሶ ቃላት፡- ቃላትን መዋስ አንዱ የቋንቋ ባህሪ ነው፡፡ አማርኛ ቋንቋም እንደሌሎች ቋንቋዎች ሁሉ ቃላትን ይዋሳል፡፡ ለምሳሌ፡- ከኦሮምኛ ቋንቋ እንደ ቀበቶ፣ ሰንጋና አባወራ ያሉትን ቃላት ሲዋስ ከእንግልዝኛ ደግሞ ቴሌቭዥን፣ ሞባይልና ኮምፒዩተር ያሉትን ወስዷል፡፡ |

**በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎች ስለተውሶ ቃላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ናቸው፡፡**

- ተማሪዎች ይህን ተግባር ከመስራታቸው በፊት ስለተውሶ ቃላት ምንነት በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የሰፈረውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመጠቀም ስለተውሶ ቃላት ምንነት ግንዛቤ እንዲያገኙ ያድርጉ፡፡
- ሌሎች ሰዎችን ጠይቀው በመምጣት ተጨማሪ የተውሶ ቃላትን ክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የተውሶ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ትኩረት ያድርጉ፡፡

1. ሀገራችን የብዙ ባህል ባለቤት ነች፡፡
2. ተባብሮ መስራት ለእድገት ጠቃሚ ነው፡፡
3. የቤት ስራችንን በአግባቡ መስራት ይጠበቅብናል፡፡
4. ጎበዝ ተማሪዎች ሁልጊዜ ትምህርታቸውን በንቃት ይከታተላሉ፡፡
5. ኢትዮጵያ የብዙ ጀግኖች አትሌቶች መፍለቂያ ሀገር ናት፡፡

**ክፍል አምስት፡- ፅህፈት**

**ተግባር አንድ፡- መፃፍ**

**መምህር፡-**

**በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል እንዲያዳብሩ የሚያግዙ ናቸው፡፡**

- ተማሪዎች ከጠዋት እስከማታ የሚያከናውኑትን ተግባር እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ‹‹ጊዜ ወርቅ ነው›› የሚለውን አባባል ከተለያዩ ሰዎች ጠይቀው በመምጣት ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ፣መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የፃፈትን ሀሳብ በመመልከት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱም ተነስተው ሌሎች ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

**ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች በዋናነት ተማሪዎች አዳምጠው መፃፍ እንዲችሉ የሚያግዙ ናቸው፡፡**

- መምህር ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ድምፅዎትን ከፍ አድርገው በማንበብ ተማሪዎቹ እያደመጡ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ከላይ በንባብ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች አዳምጠው መፃፋቸውን ያረጋግጡ፤
- ክፍተት ያለባቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ሌሎች ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡

**ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው**

**ተግባር አንድ፡- ግሶችን መለየት**

| **ማስታወሻ** |
| --- |
| ግስ፡- ግስ ሁነትን ወይም ድርጊትን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ግስ በአረፍተ ነገር መጨረሻ በመግባት አረፍተ ነገርን የሚያስር ወይም የሚቋጭ የቃል አይነት ነው፡፡<br>ምሳሌ፡-<br>ሀ. ታማኝነት የመልካም ዜጋ መገለጫ **ነው**፡፡<br>ለ. ተማሪዎች ንፅህናቸውን **ይጠብቃሉ**፡፡<br>ከዚህ በላይ በቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች ማየት እንደሚቻለው ግሶቹ በአረፍተ ነገሮቹ መጨረሻ ገብተዋል፤ የአረፍተ ነገር መቋጫም ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ‹‹ነው›› እና ‹‹ይጠብቃሉ›› የሚሉት ሁለት ቃላት ግሶች ናቸው፡፡ |

ሀ.በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ስም የሆኑ ቃላትን እንዲለዩ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ባለፈው ምዕራፍ በተማሩት መሰረት ስሞችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄውን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡

<u>መልስ</u>፡-

| **የፍራፍሬ ስሞች** | **የሃይቅ ስሞች** | **የእንስሳት ስሞች** | **የቦታ ስሞች** | **የሰው ስሞች** |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ፓፓዬ<br>መንደሪን<br>ማንጎ<br>ሎሚ | ጫሞ | ፍየል<br>በግ | ዲላ<br>አርባ ምንጭ | ሃና<br>ነስረዲን |

**ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ግሶችን እንዲለዩ የሚያስችሉ ናቸው፡፡**

- ተማሪዎች ግሶችን እንዲለዩ ከማለማመድዎ በፊት ከዚህ ቀደም ስለስም ያነሳነውን ሀሳብ በማስታወስ አያይዘው የግስን ምንነት ያስረዷቸው፡፡
- ግስን የተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያና ምሳሌዎችን በመስጠት መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በመቀጠለ በ ‹‹ለ›› እና ‹‹ሐ›› ተግባር ላይ የቀረቡትን ተግባራትን ያሠሯቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

**መ. በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ በቀረቡት ግሶች አማካኝነት አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡**

- ሁሉም ተማሪዎች የተሰጠውን ተግባር መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የሰሩትን መልስ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በቀረበው መልስ መሰረት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተግባራትን ይስጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ክትትልዎ አይለያቸው፡፡ የተማሪዎችን የመማር ብቃት ታሳቢ ያደረገ ምዘናን ይጠቀሙ፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣**

**ማጠቃለያ**

*ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ስለጊዜ አጠቃቀም አንስተው የማዳመጥ ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ በንግግር ክፍል ድግሞ የሚያውቋቸውን የመዝናኛ ቦታዎች በምልልስ መልክ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ የተለያዩ ጽሑፍችን አንብበን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡ የተውሶ ቃላትን አንስተው አረፍተ ነገሮችን መስርተዋል፡፡ በመፃፍ ክፍል የጊዜ አጠቃቀምን ምንነት በራሳችው አባባል አሳጥረው ፅፈዋል፡፡ በሰዋስው ክፍል ግሶችን የተመልከትን ሲሆን በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የገቡትን ግሶች ለይተዋል፤ አረፍተ ነገርም መስርተውባቸዋል፡፡*

*መምህር በአጠቃላይ በምዕራፉ መግቢያ ላይ የሰፈሩት አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን በመጠቀም ይፈትሹ፡፡*

- *የሚደመጡ ተግባራትን በመስጠት ያዳመጡትን በትክክል መረዳታቸውን ማረጋገጥ*
- *አንድን ምንባብ አንብበው የምንባቡን መልዕክት መረዳታቸውን መለየት*
- *በቃል እየተነገራቸው አረፍተ ነገሮችን በትክክል መፃፋቸውን ማረጋገጥ*
- *የውሰት ቃላትን መለየታቸውን መከታተል*
- *ግሶችን በአረፍተ ነገር ውስጥ መለየታቸውን ማረጋገጥ/ መለካት ይችላሉ፡፡*

# ምዕራፍ አምስት (15 ክፍለ ጊዜ)

## መጓጓዣ

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የተሰጣቸውን ምንባብ አንብበው ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- የተሰጣቸውን ምንባብ በጥልቀት በማንበብ ከተጨባጭ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡
- የስም ገላጮችን ይለያሉ፡፡
- ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች ፡-**

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

**ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር**

**የመጓጓዣ አይነቶችና አገልግሎታቸው**

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መምህር**

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለመጓጓዣ ያላቸውን የቀደመ እውቀት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የማዳመጥ ፍላጎታቸውን ለማነቃቃት በየቀኑ ስለሚጠቀሟቸው መጓጓዣዎች ይጠይቋቸው፡፡
- አተገባበሩም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ፅሐፍ ሲያነቡ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የማዳመጥ ተግባሩን ያከናውናሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በአንድ ጊዜ ነው፡፡
- ለተማሪዎቹ ምንባቡን ሁለት ጊዜ እንደሚነበብላቸው ይንገሯቸው፡፡
- ተማሪዎች እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

## የመጓጓዣ አይነቶችና አገልግሎታቸው

መጓጓዣ የሰው ልጅ ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የእንቅስቃሴ ሂደቱን ለማቅለል የሚጠቀምባቸው መገልገያዎች ናቸው፡፡ መጓጓዣዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ባህላዊ መጓጓዣዎች የሚባሉት የተለያዩ እንስሳትን በማሰልጠን የምንገለገልባቸውን እንደ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ግመል አህያ ያሉትን የጋማ ከብቶች የሚመለከት ነው፡፡ ከነዚህ የየብስ መጓጓዣዎች በተጨማሪ  ታንኳንና ጀልባን ለውሃ ላይ ትራንስፖርትም እንጠቀማለን፡፡

ዘመናዊ መጓጓዣዎች ከሳይንስና ቴክኖሎጅ መስፋፋት ጋር ተያይዘው የመጡ የትራንስፖርት መገልገያዎች ናቸው፡፡ ዘመናዊ መጓጓዣዎች እንደየደረጃቸውና አይነታቸው፣ ባላቸው ፍጥነትና ማጓጓዝ በሚችሉት ጭነት መጠን ይለያያሉ፡፡ እነዚህ መጓጓዣዎች የየብስ፣ የአየርና የውሃ ተብለው በሶስት ይከፈላሉ፡፡

### የየብስ መጓጓዣ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል ?

የየብስ መጓጓዣዎች የሚባሉት እንደመኪና፣ ባጃጅ፣ ታክሲ፣ ብስክሌት፣ አውቶቡስና ባቡር የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ የየብስ መጓጓዣዎች ለማህበረሰቡ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ይታወቃሉ፡፡ ዘመናዊ የአየር ላይ መጓጓዣዎች የምንላቸው ደግሞ አውሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ጄት ወዘተ ሲሆኑ ከየብስ መጓጓዣዎች አንፃር ሲታዩ በጣም ፈጣን ናቸው፡፡ ዘመናዊ የውሃ ላይ መጓጓዣዎች የሚባሉት ደግሞ የሞተር ጀልባና መርከብ ናቸው፡፡ መርከብ በባህር ላይ በአንድ ጊዜ ብዙ ጭነቶችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ያገለግላሉ፡፡

ዘመናዊ መጓጓዣዎች የሚሰጡት አገልግሎት መጠነ ሰፊ ቢሆንም በአግባቡ ካልተገለገልንባቸው በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም በዚሁ ምክንያት ከሚመጡ ጉዳቶች ለመጠንቀቅ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመከላከል ለእግረኞችና ለአሽከርካሪዎች የወጡ ህጎችና መመሪያዎችን በማክበር መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የሰፈሩትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል አሰሯቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ይስጡ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ለፈጣን፣ መካከለኛና ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል ላላቸው ተማሪዎች እንደየአቅማቸው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ይከታተሉ፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ ተነስተው የራሳቸውን ማብራሪያ እንዲሰጡ ያበረታቱ፡፡
- ጥሩ ተሳትፎ ላላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ግብረ መልስ ይሰጡ፡፡

**ተግባር ሁለት፡ ቃላት**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- አውዳዊ ፍቺ ከመዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንደሚለይ ይንገሯቸው፡፡

**ማስታወሻ**

አውዳዊ ፍቺ ማለት ቃሉ በገባበት አውድ ውስጥ ሆኖ የሚሰጠው ትርጉም ነው፡፡ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ማለት ደግሞ የቃሉ ፍቺ የሚሰጠው በገባበት አውድ ሳይሆን ቃሉ በያዘው ቀጥተኛ ፍቺ ነው፡፡ ይህ አይነት ፍቺ መዝገበ ቃላት ላይ ስለሚገኝ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ተብሎ ይታወቃል፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ መስራታቸውንና ለቃላቱ ትክክለኛውን አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ተጨማሪ የመለማመጃ ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡
- ሁሉንም ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተለየ ክትትልና ድጋፍ ይስጧቸው፡፡

**መልስ**፡-1. በርካታ 2. ዘርፈ ብዙ/ የተለያየ 3. የተሻለ

4. ለማጓጓዝ 5. መጠቀሚያዎች

- ሌሎች ከአውድ ጋር የሚስማሙ መልሶችንም መቀበል ይችላሉ፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣ የሚነበቡ አጫጭር ታሪኮች**

**ክፍል ሁለት፡- መናገር**

**ተግባር አንድ፡-**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመነሳት ንግግር እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎች የጥያቄዎችን መንፈስ እንዲረዱት ያድርጓቸው፡፡
- ቀጥሎም በተራ ቁጥር 3 ላይ የቀረበውን ጥያቄ ከ3-5 የሚሆኑ ተማዎችን የያዘ ቡድን እንዲመሰረት ያድርጉ፡
- ከዚያም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቡድናቸው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ከቡድኑ አባላት ውስጥ አንዱ ተወያይተው የደረሱበትን እንዲናገር ያድርጉ፡፡
- በዚህ ወቅት የንግግር ችሎታቸው ምን ያህል የዳበረ እንደሆነ ይገምግሙ፡፡
- በግምገማው መነሻነት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸው፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

**የመንገድ ደህንነት**

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**መምህር፡-**

- በመጀመሪያ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረበውን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ያሠሯቸው፡፡
- ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በሚያነቡበት ወቅት የጥሩ አንባቢ ባህሪያትን እንዲተገብሩ ይንገሯቸው፡፡

| |
|---|
| **የጥሩ አንባቢ ባህሪያት**<br>ማስታወሻ መያዝ፣ አዳዲስ ቃላትን መለየት፣ አውዳዊ ፍቺን መጠቀም፣ ድምፅ ሳያወጡ ማንበብ፣ በጣት አለመጠቆም፣ ከንፈር አለማንቀሳቀስ ወዘተ. ናቸው። |

- የጊዜ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው።
- በመጨረሻም አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ ምን ተረዳሁ የሚለውን ጥያቄ ራሳቸውን እንዲጠይቁ ያድርጓቸው።

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

**መምህር፡-**

ሀ. በተማሪ መፅሐፍ በዚሁ ተግባር ስር የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው።

ለ. በዚሁ ተግባር ስር የቀረቡትን የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች በፅሑፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው።

- ከላይ የቀረቡትን ተግባራት ያሠሯቸው።
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ይከታተሉ።
- ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች ድጋፍ አይለያቸው።
- ተማሪዎቹ ተግባራቱን ምን ያህል በትክክል እንደሰሩ የክፍል ስራ በመስጠት ይመዝኗቸው።
- ከምዘናው ውጤት ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን ይስጧቸው።

መልስ፡- 1.ሐሰት 2.እውነት 3.እውነት 4.ሐሰት

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**መምህር፡-**

ሀ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ በፅሑፍ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡- 1. የሚጓዝበት 2. ማለፍ 3. ማውራት

4. መገንዘብ 5. ጥፋት

ለ. በዚሁ ተግባር ላይ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡- 1. ለጉዳት 2. መለያ 3. እንቅስቃሴ

4. መሞት 5. ዳር

- በመጀመሪያ ስለተመሳሳይ ቃላት ፍቺና ስለአውዳዊ ፍቺ ያስታውሷቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ክትትል ይደረግላቸው፡፡
- ቀጥሎም አስፈላጊውን እርማትና ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከተሰጠው ግብረ መልስ ተነስተው ሌሎች ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡
- የተሻለ ለሰሩ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጡ፡፡

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

**መምህር፡-**

ሀ. በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

- ተማሪዎቹ ተግባሩን መከወናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት የተማሪዎችን ችሎታ ያዳብሩ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አይርሱ፡፡

ለ. ተማሪዎች በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

- ከሚያውቁት በመነሳት አረፍተ ነገሮችን እንዲያዋቅሩ ያድርጉ፡፡
- ከእለት ተእለት ልምዳቸው ተነስተው የመንገድ ላይ ጥንቃቄያቸው ምን እንደሚመስል በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛ ያድርጉ፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- ቅንጫቢ ፅሁፎች፣ አጫጭር ተረቶች፣ ሻሸ ቦርድ**

**ክፍል አራት፡- ቃላት**

**ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ**

**መምህር፡-**

ሀ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡- 1. ሐ 2. ሀ 3. ለ

4. ሠ 5. መ

ለ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡- 1. ሐ 2. ሀ 3. ለ

4. ሠ 5. መ 6. ረ

ሐ. በተማሪ መፅሐፍ ላይ የሰፈሩት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

መልስ፡- 1. ከፍተኛ 2. ተሸመ 3. ልምምድ/ጥናት

4. የበለፀገች 5. ደንቦቹን

መ. ምሳሌውን መሰረት አድርገው ጥምር ቃላትን እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡

- በአጠቃላይ ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- እርማት / ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ተጨማሪ ተግባርትን ያሰሩ፡፡
- እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ድጋፍ ያድርጉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**መምህር፡-**

ሀ. በዚህ ተግባር ስር ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላት ቅደም ተከተል በማስያዝ አስተካክለው እንዲፅፉ ያግዟቸው፡፡

- ቅደም ተከተል ከማስያዛቸው በፊት ምሳሌና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- አረፍተ ነገሮቹን በትክክል አስተካክለው መፃፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- የፅህፈት ክሂላቸውን ለማሻሻል ስለሚያግዛቸው ተደጋጋሚ ተግባራትን በመስጠት ይርዷቸው፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር ደግሞ ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

- ይህ ተግባር የፅህፈት ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ ከማገዙም በተጨማሪ አንቀፅ ወደማዋቀር ስለሚያሸጋግራቸው ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባት አስፈሊጊውን እርማትና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መፃፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- ክፍተት ላለባቸው ተማሪዎች ቀለል ያለ ተግባራትን ይስጧቸውና ልምምድ ያድርጉ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ካሉ ክትትልና ዕገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎች ቤታቸው ሄደውም የሚሰሯቸውን የመፃፍ ተግባራት ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው**

**ተግባር አንድ፡- ገላጮችን መለየት**

**መምህር፡-**

**ማስታወሻ**

**የስም ገላጮች**

ቅፅሎች የስም ገላጮች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ቅፅሎች የስም ገላጮች ናቸው ሲባል ከስም ጋር በመግባት ባህሪን፣ ቅርፅን፣ መጠንን፣ ቀለምን፣ ወገንን ወዘተ. የሚገልፁ የቃል ክፍል ናቸው፡፡ አንድን ነገር ከሌላ ነገር በቅርፁ፣ በመጠኑ፣ በቀለሙ ወዘተ. ይለያሉ፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ የሚገለፀው በቅፅል አማካኝነት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

- ባህሪን የሚገልፁ፡- ጥሩ፣ ደግ፣ የዋህ፣ ምስጉን…
- መጠንን የሚገልፁ፡- ትልቅ፣ ትንሽ፣ ብዙ፣ ጥቂት…
- ቅርፅን የሚገልፁ፡- ክብ፣ ሞላላ፣ ዝርግ፣ ጠፍጣፋ…
- ቀለምን የሚገልፁ፡- ቀይ፣ ነጭ፣ ጥቁር፣ አረንጓዴ…
- ወገንን የሚገልፁ፡- ኢትዮጵያዊ፣ ኡጋንዳዊ፣ ሱማሌያዊ… ወዘተ የመሳሰሉት ቅፅሎች ወይም የስም ገላጮች ናቸው፡፡

በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲመጡ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

- አቤሴሎም ትልቅ ቤት ገዛ፡፡
- አስቴር ኢትዮጵያዊ ዘፋኝ ነች፡፡
- ነጭ መኪና እወዳለሁ፡፡

**ሀ. በዚህ ተግባር ስር በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የስም ገላጮችን በመለየት እንዲያሰምሩባቸው ያድርጉ፡፡**

- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ድጋፍ ለሚሹት ተማሪዎች አስፈላጊውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ካሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡

**ለ. በዚህ ስር በቅፅል የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ቃላት ቀርበዋል፡፡**

- ለተማሪዎች ቃላቱ የስም ገላጭ መሆናቸውን ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲያዋቅሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይከታተሉ ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት እርማት ይስጧቸው፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ አስፈላጊው ድጋፍ አይለያቸው፡፡
- ግብረ መልስና አስፈላጊውን ምላሽ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡

በምዕራፉ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ይዘቶች የሚዳስሱ የክለሳ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዱት ለመለየት ያስችላሉ፡፡ ስለሆነም ሁሉም ተማሪዎች እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ከምእራፉ ትምህርት ያገኙትን እውቀትና ክሂል ለመገምገም ስለሚረዱ የክለሳ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማበረታታቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣**

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውሰጥ ተማሪዎች ስለመጓጓዣ አንስተዋል፡፡ በዚህም ስለባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎች በማዳመጥ ቀርበ ካደመጡ በኂላ ምንባቡን በቃል ተርከዋል፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዙ የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ እንዲሁም ስለመንገድ ላይ ደህንነት አንብበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችንም ሰርተዋል፡፡ ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡ የገላጮችን ምንነት አንስተው በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ለይተው አመልክተዋል፡፡ ለቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ፍች ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ በምዕራፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ይዘቶች መነሻ በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ መምህር የምዕራፉ አላማዎች ከግብ መድረሳቸውንም ለማረጋገጥ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ በሚከተለው መልኩ መገምገም ይቻላል፡፡

- የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው የቃል ዘገባ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ፣
- ያነበቡትን ምንባብ ከተጨባጭ ህይወታቸው ማስተሳሰራቸውን መለየት፣
- የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው መፃፋቸውን መከታተል፣
- ገላጮችን መለየታቸውን ማየት፣
- ለቃላት ትክክለኛ ፍች መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣

# ምዕራፍ ስድስት (15 ክፍለ ጊዜ)

## ስነ ምግባር

### ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ጠቃሚ ነጥቦችን ይናገራሉ፡፡
- ካነበቡት ምንባብ ውስጥ ጥሩና መጥፎ ስነ ምግባሮችን ይለያሉ፡፡
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

### የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ስዕሉን ተመልክተው የሚደመጠው ምንባብ ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ‹‹አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ›› በሚል የቀረበውን የማዳመጥ ርዕስ ስለምን ሊተርክ እንደሚችል እንዲገምቱ ያበረታቷቸው፡፡
- ታማኝነት ምን ማለት እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡
- የሚደመጠውን ምንባብ ርዕስ መሰረት በማድረግ የትኛው መልካም ወይም መጥፎ ስነምግባር እንደሆነ ካላቸው ልምድ በመነሳት ከነምክንያታቸው እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ቀደም ብሎ የሚደመጠውን ምንባብ በጽሑፍ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም ሌሎች ተማሪዎች የማዳመጥ ምንባብ ሲያዳምጡ መስማት የተሳናቸው ደግሞ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ምንባቡን ሁለት ጊዜ እንደሚያዳምጡት ለተማሪዎቹ ቀድመው ያሳውቋቸው፡፡
- ተማሪዎቹ በትኩረት እያዳመጡ በመሃል የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን ይጠይቋቸው፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩ በሚከናወንበት ወቅት ተማሪዎች በአግባቡ እያዳመጡ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡

## አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ

አንድ ቀን አንድ ሰው በመንገድ ዳር ተኝቶ አትለፉኝ፤ አትለፉኝ፤ እያለ በተደጋጋሚ ይወተውት ነበር፡፡ በመልካም ባህሪያቸው የሚታወቁት አቶ አየለ በዚያ በኩል እያለፉ እያለ የሰውየውን ድምፅ ሰምተው ወደ እርሱ ቀረቡ፡፡ ቀርበውም ‹‹ምን ሆነሃል ወንድሜ?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ አታላዩ ሰውዬም ‹‹አሞኛል፤ አሞኛል፤ እርዱኝ›› አለ በተቆራረጠ ድምፅ፡፡ ‹‹እዚህ እንደተኛሁ ሊመሽብኝ ነው፡፡ እባክዎን ይርዱኝ›› ብሎ ተማፀነ፡፡

አቶ አየለም ደግ ሰው ስለሆኑ ሰውየውን ከተኛበት በእጃቸው ደግፈው አነሱት፡፡ ‹‹ወዴት እንድወስድህ ትፈልጋለህ?›› ብለው ጠየቁት፡፡ ‹‹አታላዩ ሰውዬ ቤቴ በጣም ሩቅ ነው፡፡ እዚያ እስከምንደርስ እኩለ ሌሊት ይሆናል›› አሏቸው፡፡ አቶ አየለም ‹‹ታዲያ ምን ይሻላል›› በማለት ጠየቁት፡፡ ‹‹እርስዎ እዚህ አቅራቢያ ከሆኑ ወደቤትዎ አስጠጉኝ›› በማለት ለመናቸው፡፡ አቶ አየለ ሳያመነቱ ወደ ራሳቸው ቤት ይዘውት ሄዱ፡፡

## ከዚህ በኋላ አታላዩ ሰው ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

አቶ አየለ ቤት እንደደረሱ መሽቶ ስለነበር እራት በልተው ወደመኝታ ሄዱ፡፡ አታላዩም ሰውዬ በተዘጋጀለት መኝታ ላይ እንዲተኛ ተደረገ፡፡ አታላዩም አቶ አየለና ቤተሰቡ መተኛታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ቁሳቁሶች ሰብስቦ ሊወጣ ሲል አቶ አየለ ኮሽታ ሰምተው ከእንቅልፋቸው ነቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው አታላይ ሌባ መሆኑን ተረድተው ‹‹ስማኝ አንተ ሰው ይህንን ድርጊትህን የሰማ ሰው ሁሉ ለታመመና ለተቸገረ እርዳታ ለማድረግ ይፈራል፡፡ ስለዚህ ይህንን ድርጊትህን ሰው አይስማ›› አሉት፡፡ አታላዩ ሰውዬም በአቶ አየለ ንግግር ልቡ ተነክቶ እቃውን መልሶ ከዚያ ቤት በፍጥነት ወጣ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማታለልን እርግፍ አድርጎ ተወው ይባላል፡፡

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**መምህር፡-**

**ሀ. በዚህ ተግባር ስር በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡**

- ያዳመጡትን ምንባብ ዋና ሀሳብ በቃል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች ሚና እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ባዳመጡት ምንባብ ውስጥ የአታላዩን ሰው ድርጊቶች እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስለአታላይ ሰዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡
- በዚህ ሂደት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ፈጣን፣ መካከለኛና ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል ላላቸው ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉና መልሳቸውን እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡
- ጥሩ ተሳትፎ ላደረጉ ተማሪዎች የማበረታቻ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

**ለ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ምንባብ መሰረት ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልፁ ያበረታቱ፡፡**

- አቶ አየለ ለምን እንደተታለለ ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ታሪኩን ከራሳቸው ህይወት ጋር እያዛመደ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች መታመን ያለውን ጠቀሜታ ጠይቀው በመምጣት በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህን ተግባር እንዲሰሩ ከአንድ ቀን በፊት ቀድመው የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡
- ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በአግባቡ መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡
- ፅፈው የመጡትን የቤት ስራ  በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የእርስ በእርስ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡

- ከዚያም ትክክለኛውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ ተነስተው ከክፍል ውጭ የሚሰሩትን ተግባራት ይስጧቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- የተለያዩ አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ ጽሁፎች፣ የቃላት ቻርት...**

**ክፍል ሁለት፡- ንባብ**

**ሮዛና ሳሙኤል**

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

**መምህር፡-**

- በቅድሚያ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ንባብ ጥቄዎችን ያሰሯቸው፡፡
- የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ ሆነው እዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ሁሉም ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ከዚያም ተማሪዎቹ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ገፀ ባህሪያቱን ተከፋፍለው ሴት ተማሪዋ ሮዛን ወንድየው ተማሪ ደግሞ ሳሙኤልን በመወከል ተራ በተራ እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- የጥሩ አንባቢ ባህርያትን ተከትለው እንዲያነቡ ፍንጭ ይስጧቸው፡፡
- ቃላትንና ሀረጋትን  ትክክል መጥራታቸውን፣ አረፍተ ነገሮችን ሲያነቡ ስርዓተ ነጥቦችን እያገናዘቡ ማንበባቸውን (ለምሳሌ፡- ሀተታዊ አረፍተ ነገሮችን ሲነቡ በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ እረፍት ማድረጋቸውን፤ ጥያቄያዊ ለሆኑ አረፍተ ነገሮች ተገቢውን ድምፀት መስጠታቸውን) ወዘተ ይከታተሉ፡፡
- በሚያነቡበት ወቅት ‹‹የንባብ ጊዜ›› ጥያቄውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ከተሰጣቸው ምንባብ ውስጥ ጠቃሚ ቃላትን እንዲያወጡ ይንገሯቸው፡፡ ለምሳሌ፡- (መልካም ስነምግባርን የሚያመለክቱ)

**ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ በዚሁ ተግባር ስር የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያግዟቸው፡፡
- በምንባቡ ውስጥ ያለት ባለታሪኮች እነማን እንደሆኑ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የመልካም ስነ ምግባር ምንነትን እንዲገልፁ ያደፋፍሯቸው፡፡
- የመልካምና የመጥፎ ስነ ምግባር መገለጫዎችን እንዲዘረዝሩ ያርጓቸው፡፡
- ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ አዳዲስ ቃላት ካገኙ ለቅመው በማውጣት እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፤ በመጀመሪያ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ሌሎች ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፤ በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ይስጡ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቱ፡፡
- እገዛ ለሚፈልጉ ተማረዎች ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- ለተማሪዎች እንደየ ትምህርት አቀባበላቸው ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን እንዲያዛምዱ ያግዟቸው፡፡**

- በመጀመሪያ የክፍል ስራ ይስጧቸው
- ከዚያም ለአስር ደቂቃ በማስታወሻ ደብተራቸው በመገልበጥ መልሱን እንዲፅፉ ያድርጉ
- በመቀጠል ደብተራቸውን በማረም ትክክለኛውን መልስ እንዲፅፉ ይንገሯቸው፡፡

መልስ፡- 1. ለ 2. ሐ 3. ሠ
4. ሀ 5. መ

**ለ. በተማሪ መፅሀፍ ላይ በዚህ ተግባር ስር በሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡**

መልስ፡- 1. ትውልድ 2. ኃላፊነት 3. ስነ ምግባር

4. ይንከባከባል 5. ማገዝ

- በአጠቃላይ ከላይ በ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› የቀረቡትን ተግባራት ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ በመስጠት ለተማሪዎች ትክክለኛውን የቃላት ፍቺ ያሳውቋቸው፡፡
- ከተሰጠው ግብረ መልስ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት አይርሱ፡፡
- የተሻለ ተሳትፎ ያደረጉ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

**ተግባር ሁለት፡- መፃፍ**

**መምህር፡-**

በዚህ ተግባር ስር የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ሊያዳብሩ የሚችሉ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የፅህፈት ክሂል በሂደት የሚዳብር ነው፡፡

- ስለሆነም የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎቹ ጊዜ ወስደው እንዲለማመዱ ይፍቀዱላቸው፡፡
- ፅፈው በሚመጡት መልስ ላይም አስፈላጊውን ክትትልና እርማት በመስጠት የበለጠ የፅህፈት ክሂላቸውን የሚያዳብሩበትን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ፡፡
- መልካም ስነ ምግባር የሚጠቅመውና መጥፎ ስነ ምግባር የሚጎዳው ማንን እንደሆነ ጠይቀው ፅፈው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ፅፈው መምጣታቸውን ይከታተሉ፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎች ያለባቸውን ክፍተት እንዲያዩ ይጠቁሟቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡- አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ፣ የቃላት ቻርት፣**

**ክፍል ሶስት፡- ቃላት**

**ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ**

**መምህር፡-**

**ሀ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡**

መልስ፡-

1. ሠ 2. መ 3. ለ

4 ሐ 5. ሀ

**ለ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ከሳጥኑ ውስጥ ተስማሚ የሆኑትን ተጣማሪ ቃላት በመምረጥ እንዲያጣምሩ ይርዷቸው፡፡**

- ይህን ተግባር በክፍል ስራ መልክ በመስጠት ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ቃላቱን በሚያጣምሩበት ጊዜ የተሳሳተ ትርጉም ወይም የቋንቋውን ስርዓት ያፈረሰ እንዳይሆን ተጨማሪ ምሳሌዎችንና ማብራሪያዎችን በመስጠት ያግዟቸው፡፡
- በአጠቃላይ ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን እየተዘዋወሩ በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ከዚያም እርማት ወይም ግብረ መልስ ይስጡበት፡፡
- ቀጥሎም ከግብረ መልሱ ተነስተው ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የሚያግዙበትን ስልት ይቀይሱ፡፡ (ለምሳሌ፡- ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ በማድረግ መማማር የሚችሉበትን መንገድ ያመልክቷቸው፡፡)
- የተማሪዎቹን የትምህርት አቀባበል ከግንዛቤ በማስገባት ፈጣን፣ መካከለኛና ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል ችሎታቸውን በመለየት አስፈላጊውን ስልት በመከተል አቅማቸውን ያማከለ ተግባራት ይስጡ፡፡ (ለምሳሌ፡- ፈጣን ተማሪዎችን ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡ ደከም ላሉት ደግሞ ማጠናከሪያ በመስጠት ማበረታታት ይችላሉ፡፡)

<u>መልስ</u>፡- 1.ኋላ ቀር 2.ቁምሳጥን 3.ግንባር ቀደም 4.ቅደም ተከተል

5.ግብረ አበር 6.ህገ ደንብ 7.ልብስ ሠፊ

**ክፍል አራት፡- ፅህፈት**

**ተግባር አንድ፡- መፃፍ**

**መምህር፡-**

- ከዚህ ቀደም በምዕራፍ ሁለት ስለስርዓተ ነጥብ ማንሳታችንን በቃል በመከለስ ያስታውሷቸው፡፡
- ስርዓተ ነጥቦቹን በፅህፈት ውስጥ በሚጠቀሙበት ጊዜ ምልክቶቹን ለይተው በማወቅ በተገቢው ቦታ አስገብተው ማሳየት እንዲችሉ ማብራሪያ ይስጧቸው፡ ፡
- ይህም የፅህፈት ክሂላቸውን ለማሻሻል በሚያደርጉት ልምምድ ውስጥ እግረ መንገዳቸውን የተሟላ ሃሰብ ማስተላለፍ የሚችል ጽሑፍ እንዲያዋቅሩ ይረዳቸዋል፡፡
- ከዚያም በዚህ ክፍል ስር በ‹‹ሀ›› ና ‹‹ለ›› ላይ የቀረቡትን ተግባራት ያሰሯቸው፡፡
- የተሰጧቸውን አረፍተ ነገሮች በትክክለኛው ስርዓተ ነጥብ ማሟላታቸውን ደብተራቸውን በመመልከት ያረጋግጡ፡፡
- አሰፈላጊውን ግብረ መልስም ይሰጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት የልምምድ እድሉን ይፍጠሩላቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች አሳታፊ የሆኑ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

**ክፍል አምስት፡- ሰዋስው**

**ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ**

**መምህር፡-**

**ማስታወሻ**

ተውሳከ ግስ፡- የግስ ጭማሪ ማለት ነው፡፡ ከግስ ጋር እየገቡ ግሱ የሚገልፀውን ድርጊት እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ በምን ሁኔታ እንደተፈፀመ ይገልፃሉ፡፡ መደበኛ ተውሳከ ግስ የሚባሉት ጥቂት ናቸው፡፡
እነሱም፡- ክፉኛ፣ ምንኛ፣ ጅልኛ፣ ቶሎ፣ ገና ያሉት ናቸው፡፡ ሌሎች በተውሳከ ግስነት የምንጠቀምባቸው ቃላት አሉ፡፡ ተውሳከ ግሶች ከሌሎች ቃላት የሚለዩት በአብዛኛው በአገባባቸው ነው፡፡ ሁሉም ግስን እየቀደሙ ይገባሉ፡፡

እንደሌሎች የቃል ክፍሎች ሁሉ ተውሳከ ግስም የተለያዩ ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው ፡፡

1. የጊዜ ተውሳከ ግስ
2. የቦታ ተውሳከ ግስ
3. የመጠን ተውሳከ ግስ
4. የሁኔታ ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡ ባዬ ይማም፡፡ (2004 ዓ.ም፣ 73-75)

**በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ተውሳከ ግሳዊ ቃላት እንዲለዩ ያበረታቱ፡፡**

- በመጀመሪያ ከዚህ ቀደም በሰዋስው ይዘቶች ስር የተነሱትን እንደ ስም፣ ግስ፣ ቅፅል ያሉትን የቃል ክፍሎች ያስታውሷቸው፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የተውሳከ ግስ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚለዩበት ጊዜ አብረው ስለሚያገኟቸው ብዥታ እንዳይፈጠርባቸው ያግዛቸዋል፡፡

- ተውሳከ ግስን አስመልክቶ በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ ከቀረበው ማስታወሻ በተጨማሪ ለደረጃቸው በሚመጥን መልኩ ምሳሌዎችንና ማብራሪያዎችን በመስጠት ራሳቸውን ችለው ቃላቱን የሚለዩበትን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ።
- በማስከተልም በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን ተግባራት የክፍል ስራ በመስጠት ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ያበረታቷቸው።
- በየግላቸው መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ።
- እርማት በመስጠት ክፍተት ባለበት ቦታ ግብረ መልስ በመስጠት ግንዛቤ ያስጨብጡ።
- ተጨማሪ የተግባር ልምምዶችን በቤት ስራ መልክ በመስጠት ይዘቱን የበለጠ እንዲለዩት ያግዟቸው።
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

**መርጃ መሳሪያ፡- አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ፣ የቃላት ቻርት፣ ሻሸ ቦርድ የሰዋስው ማጠራቀሚያ**

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ስለመልካምና ስለመጥፎ ስነ ምግባር በተረት መልክ የቀረበውን ጽሑፍ አዳምጠዋል፡፡ እንዲሁም በምልልስ መልክ አንብበዋል፡፡ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በራሳችን አገላለፅ ፅፈዋል፡፡ ጥሩና መጥፎ ስነ ምግባርን ለይተዋል፡፡ ስርዓተ ነጥቦችን አስመልክቶ አራት ነጥብ፣ ጥያቄ ምልክት፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ቃለ አጋኖና ትዕምርተ ጥቅስን በአረፍተ ነገር ውስጥ አስገብተው ተጠቅመዋል፡፡ ለቃላት ተቃራኒ ፍች ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ስለተውሰከ ግስ ምንነት አንስተው ቃሉን በአረፍተ ነገር ውሰጥ በመጠቀም ለይተው አመልክተዋል፡፡

የምዕራፉን ዋና ዋና ይዘቶች መነሻ በማድረግም የክለሳ ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡ መምሀር የምዕራፉ አላማዎች መሳካታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የግምገማ ስልቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ጠቃሚ ነጥቦችን በቃል መተረካቸውን ያረጋግጡ፤
- ካነበቡት ምንባብ ውስጥ ጥሩና መጥፎ ስነምግባሮችን ለይተው መፃፋቸውን ይፈትሹ፤
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይለዩ፤
- ለቃላት ትክክለኛውን ፍቺ መስጠታቸውን ይመልከቱ፤
- ተውሳከ ግሶችን ለይተው ማመልከታቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ምዕራፍ ሰባት (15 ክፍለ ጊዜ)

### ግብርና

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚና ጨዋታ ይጫወታሉ፡፡
- ካነበቡት አንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ለይተው ይፅፋሉ፡፡
- ካነበቡት ምንባብ ውስጥ ያገኙትን ዋና ጉዳይ ይፅፋሉ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ከፅሁፍ ውስጥ ተውሳከ ግሶችን ይለያሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

- የከተማ ግብርና
- ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ለተማሪዎቹ ከማስደመጥዎ በፊት ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ርዕሱን ተመልክተው ስለምን ሊያዳምጡ እንደሚችሉ ይጠይቋቸውና የራሳቸውን ግምት እንዲያስቀምጡ ያደፋፍሯቸው፡፡
- የተማሪዎችን የማዳመጥ ጉጉት ለመጨመር ርእሱን አንብበው የቀድመ እውቀታቸውን እንዲያጋሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹን አስቀድመው ከማስደመጥዎ በፊት መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚደመጠውን ምንባብ በጽሑፍ ይስጧቸው፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ሰዓት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡
- ለእለቱ የተዘጋጀውን የማዳመጥ ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ሌላ ማስደመጥ የሚቻልበት አማራጮች ካልዎት መጠቀም ይችላሉ፡፡ (ለምሳሌ፡- አስቀድመው ድምፅዎትን በመቅዳት)
- ተማሪዎች በአግባቡ እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡
- ሰዋስው

የከተማ ግብርና

በምንኖርበት አካባቢ ከሚከናወኑ በርካታ ተግባራት ውስጥ አንዱ የከተማ ግብርና ነው፡፡በዚህ ዘርፍም የተለያዩ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የጓሮ አትክልት ማልማት፣የእንስሳት እርባታ፣የእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ፣ ጫጩት ማሳደግ፣ የማር ምርትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ የእነዚህን የግብርና ስራዎች ምርታማነት ለማሳደግ የግብርና ቢሮ በልዩ ትኩረት በዘርፉ ለተሰማሩት አካላት ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የጓሮ አትክልት ባለን ትንሽ ቦታ ላይ በማልማት ተጠቃሚ መሆን እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡-እንደ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ካሮት፣ ሽንኩርት የመሳሰለትን ማልማት እንችላለን፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን አትክልቶች በቀላሉ በግቢያችን ውስጥ በማልማት ለምግብ ፍጆታችን መጠቀም እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ከምግብ ፍጆታ የተረፈንን ሸጠን ለኑሯችን የሚያስፈልጉንን ጉዳዮች ማሟላት እንችላለን፡፡

የጓሮ አትክልት ምርታማነት ለማሳደግ የግብርና ባለሙያዎችን ምክር መውሰድ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ምክንያቱም የግብርና ባለሙያዎች የጓሮ አትክልት ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ የተሻሻሉ ዘዴዎችን፣ ዘመናዊ የግብርና መገልገያ መሳሪያዎችን፣ የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን መጠቀም እንድንችል ጠቃሚ ምክር ስለሚሰጡን ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ የመስኖ ውሃውን ተጠቅመን የጓሮ አትክልቶችን የምናለማበትን ዘዴ ይነግሩናል፡፡ስለሆነም ከግብርና ባለሙያዎች ጋር በቅርበት አብሮ መስራት ለምርታችን ማደግ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

በከተማ ውስጥ ከጓሮ አትክልት በተጨማሪ ምን ምን ነገሮችን መስራት ይቻላል ?

እንደ ደቡብ ክልል በከተሞችና በከተሞች ዙሪያ ለግቢ ማስዋቢያና ለጥላ ተብለው የሚተከሉ የፍራፍሬ ዛፎች እንደ አቦካዶ ፣ ማንጎ ፣ አናናስ ፣ ሙዝ ካዝሚርና የመሳሰሉት ደግሞ ተጨማሪ ምርትና ገቢ የሚያስገኙ ናቸው፡፡በዚህ ረገድ ከተሞች ከሚያገኙት የፍራፍሬ ምርት በምግብ አቅርቦት አኳያ ተጨማሪ ግብዓትን ያቀርባሉ፡፡

ሌላው በእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ ላይ የሚሰማሩ ሰዎችም በርካታ እንቁላል ለከተማው ነዋሪዎች ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ሁላችንም በየሰፈራችን ባሉት ሱቆች እንቁላል ብንፈልግ በቅርበት ማግኘት እንችላለን፡፡በአጠቃላይ ባለን

ትንሽ ቦታ ሊይ የጓሮ አትክልቶችንና ሌሎችን የግብርና ምርቶችን በማልማትና በመስራት የምግብ ፌጆታችንንም ሆነ ገቢያችንን በማሳደግ ኑሯችንን ማሻሻል እንችላለን

ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

መምህር፡-

**ሀ**.በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ለመለየት የተዘጋጁ ናቸው፡፡ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የማዳመጥ ምንባብ ወይም ጽሑፍ በሚገባ ማድመጣቸውን ለመለየት ምንባቡ ያቀረበበትን አደረጃጀት መነሻ በማድረግ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተማሪዎቹ ስለከተማ ግብርና አዳምጠው ከራሳቸው ተጨባጭ የህይወት ልምድ ጋር በማስተሳሰር ለጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

ከከተማ ግብርና የሚገኘውን ጥቅም ይጠይቋቸውና እርስ በእርስ እንዲነጋገሩበት ሰዓት ወስነው ይስጧቸው፡፡

- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ መልሳቸውን በጽሑፍ ይቀበሏቸው፡፡
- ተማሪዎችን እንደየትምህርት አቀባበላቸው በመለየት አስፌላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡ ፡
- የመማር ማስተማር ሂደቱ ሁለንም ተማሪዎች አሳታፊ የሚያደርግ እንዲሆን የበኩልዎን ጥረት ያድርጉ፡፡
- ጥሩ ተሳትፎ ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት የራስዎን ግብረ መልስ በመስጠት ጠቅለል ያለ ግንዛቤን ያስጨብጧቸው፡፡

**ለ**. ይህን ተግባር ለመስራት በቅድሚያ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

- ተማሪዎች ያዳመጡትን ምንባብ መነሻ በማድረግ አካባቢያቸውን የበለጠ እንዲረዱ ስለሚያስችላቸው የሚያቀርቡትን መልስ በምክንያት አስደግፈው መፃፋቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- ለመኖር መሰረታዊ ከሆኑት ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ምግብ ነው፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃዎችን ሰብስበው ፅፈው እንዲመጡ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች በጽሑፍ እንረዲያቀርቡ የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሰርተው መምጣቸውን ደብተራቸውን በመመልከት ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የቤት ስራውን መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ መልሳቸውን በቃል መቀበል ይችላሉ፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙትም ሌሎች የፅህፈት ክሂልን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡
- ተግባር ሁለት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ከፍ ሊየደርጉ የሚችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በሚከተለው መልኩ ያሰሯቸው፡፡

ተማሪዎቹ ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ አዳዲስ ናቸው ያሏቸውን ቃላት ለቅመው በማውጣት በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡

ለእነዚህ ለዘረዘሯቸው ቃላትም ተገቢውን ፍች እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

- በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት በስሩ ከተዘረዘሩት ቃላት ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን መርጠው እንዲያዛምዱ የክፍል ስራ ይስጧቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የክፍል ስራውን መስራታቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- ቃላቱን በትክክል ማዛመዳቸውን በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ክፍተት ባለበት ቦታ ተገቢውን መልስ ይንገሯቸው፡፡
- ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛዎት አይለያቸው፡፡

  መልስ፡-

  1. ምርታማ 2. ማረስረስ 3. ማሳ 4. ማጠራቀም

  5. ዘዴ 6. ድርሻ 7. የውሃ ማስተላለፊያ 8. ሰብል

ለ.በዚህ ተግባር ስር ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገሮችን እንዱመሰርቱ የሚያስችላቸው ተግባር ሰፍሯል፡፡እርስዎም የሚከተለውን ሂደት በመከተል ተግባሩን እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡

- ተማሪዎቹ ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የክፍል ስራ ይስጧቸው፡፡
- ቃላቱን በትክክል ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ይከታተሉ፡፡
- በምዕራፍ ስድስት ላይ ያነሳናቸውን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በቃል ያስታውሷቸው፡፡ ከዚም ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- አስፈላጊውን እርማት ለተማሪዎቹ ይስጡ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች መስራታቸውንም ያረጋግጡ፡፡
- ድጋፍ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ክትትል ያርጉላቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- በመጨረሻም ሌሎች ተግባራትን ይስጧቸውና እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
  መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ሰንጠረዥ፣ ሻሽ ቦርድ፣ ቅንጫቢ ፅሁፎች

ክፍል ሁለት፡- ንግግር

ተግባር አንድ፡- መናገር

መምህር፡-

ይህ ክፍል በዋናነት የንግግር ክሂልን ለማሻሻል የሚረዳ በመሆኑ የተለያዩ ተግባራትን መጠቀም አስፈሊጊ ነው፡፡

- እንደመነሻ በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ ምህረትና አህመድ የተባሉ ገፀ ባህሪያት ምልልስ የሰፈረ ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይ አቀራረብና ይዘት ያላቸው ተግባራትን ሰጥተው ማሰራት ይችላሉ፡፡
- አተገባበሩም በመጀመሪያ ተማሪዎችን ከተቻለ ወንድና ሴት በማድረግ በጥንድ በጥንድ ያደራጇቸው፡፡ ካልሆነ ግን የፆታ ስብጥሩን ባይጠብቅም በጥንድ በጥንድ እንዲነጋገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ጥንድ ጥንድ ሆነው የተደራጁት ተማሪዎች ቀደም ብለው ሚናቸውን (አንደኛው ተማሪ የምህረትን ሌላኛው ደግሞ የአህመድን) ወስደው እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- የተለማመዱትን እየወጡ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የሚሳተፉበትን እድል ያመቻቹ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈሊጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

ለምሳሌ፡- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡)

- ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች ችልታቸውን የሚያወጡበት እድል ይፍጠሩላቸው፡፡ (ለአብነት ያህል፡- በተማሪዎች መፅሀፍ ከቀረበው በዛ ያለ ገፀ ባህሪያትን ያካተተ፤ ረዘም ያለ ቃለ ምልልስ ያለው) ጽሑፍ ሰጥተው ማሰራት ይችላሉ፡፡
- ምልከታ በማድረግ አቀራረቡን መመዘን ይችላሉ፡፡
- ከዚሁ ምዘና በመነሳትም ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ያሰሯቸው፡፡

ክፍል ሶስት፡- ንባብ

አይበገሬዎቹ እህትማማቾች

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

መምህር፡-

- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት ንባቡን በንቃት እንዲያነቡ መንገድ ይክፈቱላቸው፡፡
- ጥያቄዎቹን ከራሳቸው ህይወት ጋር እያዛመዱ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ርዕሱን ተመልክተው ስለምን ሊያነቡ እንደሆነ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠል ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡
- በሚያነቡበት ወቅት የጥሩ አንባቢ ባህሪያትን እንዲያከናውኑ ያስታውሷቸው፡፡ የጥሩ አንባቢ ባህሪያትን ምንነት ካለፉት የመምህሩ መምሪያ ምዕራፍች ላይ ተገልፀዋል፡፡
- ተማሪዎች በሚነቡበት ወቅት የጊዜ ንባብ ጥያቄውን በመስራት ትኩረታቸውን በንባቡ ላይ እንዲያርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካለ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ምንባቡ የሚደርስበትን መንገድ ያመቻቹ፡፡
- በመጨረሻም ከምንባቡ የተረደትን ዋና ዋና ሀሳብ እንደሚናገሩ ያሳውቋቸው፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት፡-

መምህር፡-

**ሀ**. በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በቃል እንዲናገሩ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

- ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በቃላቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ በቀጥታ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አንድምታዊ ምላሾችን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍዎት አይለያቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ጥያቄዎቹ በድምፅ ተቀርፆ ወይም በብሬል ተፅፎ እንዲደርሳቸው ያድርጉ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው የሚማሩበትን ሁኔታ ያመቻቹላቸው፡፡
- ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ ተነስተው ተጨማሪ ተግባራትን ማሰራት ይችላሉ፡፡

**ለ.** በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት ብለው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

- በመጀመሪያ ተማሪዎች በክፍል ስራ አማካኝነት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- እውነት ወይም ሀሰት ብለው ከመለሱ በኋላ ምክንያታቸውን እንዲያካትቱ ያድርጉ፡፡
- ቀጥሎም ሁሉም ተማሪዎች ደብተራቸውን ከተቀያየሩ በኋላ የቢጤ እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን በብሬይል ፅፈው እንዲያነቡ በማድረግ መልሳቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡
- ከቢጤ እርማት በኋላ ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ይስጡ፡፡
- ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው የሚማሩበትን ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ፡፡

**ሐ**. በዚህ ክፍል ፅህፈትን ለማስተማር የተዘጋጁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

- ተማሪዎች ‹‹አይበገሬዎቹ እህትማማቾች›› በሚል የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያውን አንቀፅ ተመልሰው እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም የአንቀፁን ዋና ሀሳብ አሳጥረው እንዲፅፉ ይንገሯቸው፡፡
- ሴት ተማሪዎች የሚሳተፉባቸውን የግብርና ስራዎች ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው እንዲጽፉ በቤት ስራ መልክ ይስጧቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ሰርተው መምጣታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ያዘጋጁትን ጽሑፍ በምልከታና ክፍል ውስጥ ፅፈው ያመጡትን አንዲያነቡ በማድረግ ይገምግሙ፡፡
- ከግምገማው ተነስተው የተስተዋሉ ጉድለቶችን በመንገር እንዲስተካክል ያድርጓቸው፡፡
- የተሻለ ለሰሩ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጧቸው፡
- በአጠቃላይ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የሰሩትን ስራ በማየት ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ሁለንም ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው አሳታፊ የሆነ የማስተማር ስልትን ይከተሉ፡፡ (ይህም ሲባል ለፈጣን ተማሪዎች ከበድ ያለ ተግባራትን ሲሰጡ ዝቅተኛ ትምህርት አቀባበል ላላቸው ተማሪዎች ደግሞ አጥጋቢ የመማር ብቃትን የሚያሳኩበትን ወይም በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ተግባር ደጋግመው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡)

ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፡-

- በዚህ ተግባር ስር በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበብን አንዲማሩበት የቀረበ ነው፡፡
- ስለሆነም ያቀላጥፎ ማንበብ ስልቶችን (በጥንድ፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ፣ የህብረት፣ መሚቶ…) ተከትለው እንዲያነቡ ሁሉም ተማሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን ይፍጠሩ፡፡
- አቀራረቡም ተማሪዎች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዱያነቡ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ማንበባቸውን በማዳመጥ ማወቅ ይቻላል፡፡

- ስለሆነም በዚህ ሂደት ቃላትን በትክክል መጥራት የማይችሉ፣ አረፍተ ነገርን በተገቢው ፍጥነት የማያነቡና እንደየአረፍተ ነገሩ አይነት ተገቢውን ድምፀት እየተጠቀሙ የማያነቡ ተማሪዎችን በመለየት ተጨማሪ ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- በትክክለኛው ድምፀት የማንበብ ጉድለት ካለ እርስዎ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው፡፡
- በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ በፅሞና እንዲከታተለ ያድርጓቸው፡፡
- ይህን ተግባር ሁሉም ተማሪዎች እንዲተገብሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍ ያድርጉ፡፡

ተግባር ሶስት፡- ቃላት

መምህር፡-

- ይህ ተግባር የሚከናወነው የቃላት ፍችን ለማስተማር ሲሆን አቀራረቡም በመጀመሪያ አውዳዊ ፍች ከሌሎች ፍች እንደሚለዩ ያስታውሷቸው፡፡ ይህም ሲባል የቃል ትርጉም የሚወሰነው በገባበት አውድ መሆኑን ከነገሩ በኋላ ተግባሩን በክፍል ስራ መልክ ሰጥተው ሊያሰሯቸው ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ከገለበጡ በኋላ በማስከተል መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች መስራታቸውን ከትትል ያድርጉላቸው፡፡
- በመቀጠል ደብተራቸውን በማረም ግምገማ ያካሂዱ፡፡
- ከዚያም ግምገማውን መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ትከረት በማድረግ እንደየትምህርት አቀባበላቸውና እንደሚፈልጉት ድጋፍ ለይተው ተገቢውን ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

  መልስ፡-

  1. ሁልጊዜ　　2. አቃታቸው　　3. ተፈጠረ
  4. ድርቅ/ መቅሰፍት　　5. ረዳቸው　　6. የተጣለ

ተግባር አራት፡- መፃፍ

መምህር፡-

- በመጀመሪያ በዚህ ስር የቀረበውን ተግባር ተማሪዎቹ በቤት ስራ መልክ እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡
- የፃፉትንም ተራ በተራ እየወጡ እንዲያቀርቡ በማድረግ መገምገም ይችላሉ፡፡
- ከግምገማው በመነሳት እርማት ይስጡ፡፡
- በመጨረሻም ይህ ተግባር የመፃፍ ክህሎትን ለማዳበር የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች ይህንኑ ክህሎት ለያዳብሩ የሚችሉበትን ተጨማሪ ተግባራት በመስጠት ማለማመድ ይችላሉ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ሻሽ ቦርድ፣

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች አንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በመፃፍ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በቅድሚያ በየግላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም እየተዘዋወሩ ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ቅድሚያ ለሰሩ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈሊጊውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

መልስ፡-

1. ሐ.  2. ሀ  3. ሠ  4. ሰ

5. ለ  6. መ  7. ረ

ለ. በዚህኛው ተግባር ስር ለተቃራኒ ቃላት ፍች እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች በጽሑፍ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ደጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን እርማት በመስጠት ትክክለኛውን መልስ እንደይዙ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡-

1. ሐ  2. ሀ  3. ለ  4. ሠ  5. መ

ሐ. በዚህ ተግባር ስር በቀረቡት ቃላት ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ለይተው እንዲያሰምሩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ ለተማሪዎች ስለቅጥያ ምንነት ለክፍል ደረጃው የሚመጥን አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ተጨማሪ ምሳሌዎችን ከሰጧቸው በኋላ ተግባራቱን በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ቅጥያዎችን ለይተው እንዲያሰምሩ ይንገሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ይህን ተግባር በሚሰሩበት ሰዓት ትኩረት በመስጠት ይከታተሉ፡፡
- እገዛ ለሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎች እንደዬትምህርት አቀባበላቸው አስፈላጊውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ተግባራቱን የሚሰሩበትን መንገድ ያመቻቹላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

**መ. ተማሪዎች ከቃላቱ ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ከቃላቱ ለይተው እንዲያመለክቱ ያግዟቸው፡፡**

- ቅጥያዎችን ከቃላት ለይተው በሚያወጡበት ጊዜ የቅጥያ ምልክት (-) ማስገባት እንዳይዘነጉ ያስታወሷቸው፡፡
- ቅጥያዎቹን በትክክል ከቃላቱ ለይተው ማመልከታቸውን ያረጋግጡ፤ በመጨረሻም የራስዎን ትክክለኛ ግበረ መልስ ይስጧቸው፡

ክፍል አራት፡- ሰዋስው

ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ

መምህር፡-

ሀ. ቀደም ሲል ባነሳናቸው ምዕራፍች ውስጥ ስለ ስም፣ ስም ገላጭ፣ ግስ፣ የግስ ገላጭ አይተናል፡፡ እነዚህን የተዘረዘሩትን የቃል ክፍሎች ተማሪዎችን በድጋሚ ያስታወሷቸው፡፡ ይህም እነዚህ የቃል ክፍሎች በአረፍተ ነገሮች ውስጥ በሚመጡበት ጊዜ ቃልን ከመለየት ባለፈ አገባቡንም በሂደት እየለዩ ስለሚሄዱ ለማስገንዘብ የእርስዎ ጥረት ይታከልበት፡፡

- በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበው ተግባር በአረፍተ ነገር ውሰጥ የሚገኙትን ስም፣ ስም ገላጭ፣ ግስ፣ የግስ ገላጭ ለይተው እንዲፅፉ ነው፡፡ስለሆነም ይህን ተግባር የቤት ስራ በመስጠት ለይተው ፅፈው እንዲያመለክቱ ይንገሯቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች የቤት ስራውን ሰርተው መምጣታቸውንና በትክክል ለይተው መፃፋቸውን ደብተራቸውን በማየት ያረጋግጡ፡፡
- በመጫረሻም የራስዎን ግብረ መልስ ይስጡበት፡፡

**ለ. በዚህ ተግባር ስር እስከ አሁን የተመለከትናቸው የቃል ክፍሎች በየምድባቸው እንዲያስቀምጡ ያግዛል፡፡**

- በአዛምድ የቀረቡትን ቃላት በትክክለኛው የቃል ክፍላቸው ማዛመዳቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካለ ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- የተማሪዎች መልስ ዞረው ከተመለከቱ በኋላ አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- በዚህ ስር የቀረቡት ቃላት የግስ ገላጮች ሲሆኑ ቃላቱን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰረቱ ያድርጓቸው፡፡
- ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን መመስረታቸውን ይከታተለ፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ያግዟቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- አረፍተ ነገሮችን በሚያዋቅሩበት ወቅት ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀማቸውን ይከታተሉ፡፡
- ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- በመጨረሻም አስፈሊጊ ሆኖ ካገኙት ተጨማሪ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

*ማጠቃለያ*

*በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ስለግብርና የሚያወሱ ፅሁፎችን አዳምጠዋል። ያዳመጡትን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ የሚና ጨዋታ በመውሰድ ጥንድ ጥንድ በመሆን ንግግር አድርገዋል። ምንባብ ካነበቡ በኋላ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ሰርተዋል። በምንባቡ ውስጥ የተካተቱትን አንቀጾች ዋና ሀሳብ ለይተው ፅፈዋል። ተውሳከ ግሶችን ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ለይተው አመልክተዋል። በምዕራፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ይዘቶች መነሻ በማድረግም የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች ሰርተዋል።*

*መመህር በአጠቃላይ የምዕራፉን ዋና ዋና አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይገምግሙ።*

- *የአዳመጡትን ምንባብ መነሻ በማድረግ የሚና ጨዋታ ማድረጋቸውን በማረጋገጥ፤*
- *የአንቀጾችን ዋና ዋና ሀሳቦች ለይተው መፃፋቸውን በማየት፤*
- *የምንባቡን ዋና ሀሳብ ለይተው መፃፋቸውን በመለየት፤*
- *ተውሳከ ግሶችን ከአረፍተነገሮች ውስጥ ለይተው ማመልከታቸውን በመረጋገጥ ግምገማዎችን ያከናውኑ።*

# ምዕራፍ ስምንት (15 ክፍለ ጊዜ)

## ስራ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- አዲምጠው በምንባቡ የተነሱ ጉዳዮች ላይ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡
- ምንባብ አንብበው መልዕክቱን ይረዳሉ፡፡
- የወደፊት እቅዳቸውን ይፅፋሉ፡፡
- ለአዲዱስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ተያያዥነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ይመሰርታሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

- ታታሪው ሰራተኛ
- ቅድመ ማደመጥ ጥያቄዎች

  መምህር፡-
- በተማሪዎች መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ምንባቡን ከማስደመጥዎ በፊት ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ከዚያም ግምታቸውን ከሚያዳምጡት ምንባብ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት እንዲያስተውሉ ይንገሯቸው፡፡

ይህም በጊዜ ማዳመጥ ወቅት ተጨማሪ መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል፤ በማዳመጥ ተግባሩም ንቁ አድማጭ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ክህሎታቸውንም በሚገባ ማሳደግ እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡

- የማዳመጥ ተግባሩ ለምን ያህል ጊዜ (ሁለት ጊዜ) ያህል እንደሚከውኑት ይንገሯቸው፡፡
- በማዳመጥ ሂደት ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙ ይንገሯቸው፡፡
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ምንባቡን ቀድመው በጽሑፍ እንዲያገኙ በማድረግ ያግዟቸው፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩ በሚከናወንበት ወቅት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምንባብ እንዱያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ለሌሎች ተማሪዎች ደግሞ በመቅረፀ ድምፅ በመቅረፅ ማስደመጥ ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎቹ በንቃት እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥና ቀጣይም የሚመጣውን ታሪክ ለመገመት ያስችላቸው ዘንድ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን ይጠይቋቸው፡፡

ታታሪው ሰራተኛ

መንሱር የተወለደው በወራቤ ከተማ ነው፡፡ አባቱ አቶ ሃሚድ ቀበሌ 01 የወፍጮ ቤት ሰራተኛ ሲሆኑ እናቱ ወይዘሮ ዘምዘም ደግሞ የቤት እመቤት ናቸው፡፡

አቶ ሀሚድ የእለት ገቢያቸው እጅግ ዝቅተኛ ቢሆንም የአራት ልጆች አባት ናቸው፡፡ መንሱር አራተኛ ልጃቸው ነው፡፡ ሁለም ልጆች ትምህርታቸውን ገና ሶስተኛና አራተኛ ክፍሎች ላይ ነው በችግር ምክንያት ያቋረጡት፡፡ የአባታቸው ገቢ ለቤተሰቡ ከእለት ጉርስ አልፎ ለትምህርት አልበቃ ሲለው ሁለም ልጆች አቋርጠው ስራ ፍለጋ ወጡ፡፡

ከሁለም ልጆች የተለየ የሆነው መንሱር ግን ያገኘውን ስራ ሁልጊዜ ሳይንቅ በትጋት ይሰራል፡፡ ባገኛትም ትንሽ ገቢ አቅሙ በፈቀደ መጠን ወላጆቹን ይደጉም ነበር፡፡ ምንም እንኳን ትምህርቱን ባይጨርስም እያደገ ሲመጣም አንዱ ቀን የራሱ የሆነ ትልቅ ድርጅት ሊኖረው እንደሚችል ተስፋ ሰንቆ ነበር፡፡

መንሱር ከዚህ በኋላ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል ?

መንሱርም እንደ ጫማ መጥረግ፣ መላላክ፣ ውሃ መቅዳት፣ ያሉትን ስራዎችን ሳይንቅ ስለሚሰራ የአካባቢው ሰዎች በጣም ይወዱታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ታማኝ፣ ትሁት፣ ቁም ነገረኛ፣ ሰውንና ስራውን አክባሪ ስለነበር ለስራ የማይፈልገው የአካባቢው ሰው አልነበረም፡፡

መንሱር እያደገ ሲሄድም ጥቃቅን ስራዎችን ሰርቶ ባጠራቀማት ገንዘብ ትንሽ ሸራ ጋርዶ የንግድ ስራ ጀመረ፡፡ ጎን ለጎንም አቋርጦ የነበረውን ትምህርቱን በመቀጠል ጠንክሮ እያነበበ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ጀመረ፡፡ ንግዱም ቀስ በቀስ እየተስፋፋ ሲሄድ ሸራውን ትቶ አነስ ያለች ሱቅ ተከራይቶ መስራቱን ቀጠለ፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላም የታወቀ የሸቀጣ ሸቀጥ ነጋዴ ሆኖ ብዙ ገንዘብ ማግኘት ቻለ፡፡

በኋላም በልጅነቱ ያስበው የነበረውን የሸቀጥ ንግድ ወደ ማከፋፈያ ሱቅ አሳደገው፡፡ ከዚያም በወራቤ ከተማ የተለያዩ ቅርንጫፎችን ከፍቶ መስራት ጀመረ፡፡ በወራቤ ከተማ ዋና አከፋፋይ ከሚባሉ ነጋዴዎች ውስጥ አንዱ ሆነ፤ ወላጆቹንና ወንድሞቹንም በጥሩ ሁኔታ መርዳት ቻለ፡፡ መንሱር አሁን እድሜው 28 ዓመት ሲሆን ፍቅረኛውን ናባትን አግብቶ የአንድ ልጅ አባት ለመሆን ችሏል፡፡

ምንጭ፡ - አላምረው ገ / ማሪያም፣ (2002 ) የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ ተሻሽሎ የተወሰደ

ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. ይህ ተግባር በዋናነት የተዘጋጀው የአዳምጦ መረዳት ክሂልን ማዳበር እንዲያስችል ሲሆን ዝርዝር ተግባራቱን እንደሚከተለው ያሰሯቸው፡፡

- በመጀመሪያ ቀደም ሲል በቅድመ ማዳመጥ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ምን ያህል እንደተዛመደ በመጠየቅ ምላሻቸውን በቃል ይቀበሏቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውን ያረጋግጡ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ተግባሩን መፅሀፍ እንዲያሰፍሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹን እንደየትምህርት አቀባበላቸው በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች አሳታፉ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፍጠሩ፡፡
- ምዘናን በተመለከተ ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን እንዲናገሩ በማድረግ መመዘን ይችላሉ፡፡
- በዚሁም መነሻነት ግብረ መልሱን በመስጠት ተማሪዎችን ያበረታቱ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- አቀራረቡም የክፍል ስራ ወይም የቤት ስራን በመስጠት በማሳታወሻ ደብተራቸው ሊይ ሰርተው እንዱመጡ ይዘዟቸው፡፡
- ከዚያም እርስ በእርሳቸው የማስታወሻ ደብተራቸውን በመቀያየር እርማት እንዲሰጣጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን መስራታቸውን ክትትል በማድረግ ያረጋግጡ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ አስፈላጊው ክትትል ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ እንደየትምህርት አቀባበላቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት ማገዝ ይችላሉ፡፡
- በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

መልስ፡-

1. ባህል  2. ታላላቆቻቸውን

3. ነገ  4. ሀላፊነት

5. ስፖርት  6. ውይይት

መርጃ መሳሪያ፡- የተለያዩ አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢዎች፣ የቃላት ቻርት

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከብራል

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

መምህር፡-

- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት በመፅሀፋቸው ላይ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን ከራሳቸው ህይወት ጋር በማቆራኘት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- የጊዜ ምንባቡን ጥያቄ በማሰራት አትኩሮታቸውን በንባቡ ላይ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች በአግባቡ እያነበቡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ክትትል ያድርጉ፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው እገዛ በማድረግ የማንበብ ሂደቱ የተቃና እንዲሆን ያድርጉ፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ምንባቡ በብሬል ወይም በመቅረፅ ድምፅ ተቀድቶ እንዲደርሳቸው ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ከምንባቡ የተረደትን ዋና ሀሳብ በመጠየቅ እጃቸውን እያወጡ እንደሚመልሱ ይንገሯቸው፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

መምህር፡-

**ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡**

- ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ እንዲሳተፉ ያድርጓቸው፡፡
- በአንደምታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በማድረግ የአንብቦ መረዳት ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ከራሳቸው ህይወት ጋር አዛምደው እንዲመልሱ የሰው ልጅ በአለም ላይ ሲኖር ስራ መስራት አለበት ወይ በማለት ጠይቀው መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡

- ሰዎች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው እንኳ ለምን ሊከስሩ እንደሚችሉ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን በምክንያት እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው፡፡
- ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እንደዬፍላጎታቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲያነቡላቸው በማድረግ እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ደግሞ መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ በማድረግ ማበረታታት ይችላሉ፡፡
- በአጠቃላይ ከምላሻቸው በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱም ተነስተው የተስተዋለ ክፍተቶችን መሙላት የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

**ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት አቅም ለመለየት ያስችላሉ፡፡**

- በቅድሚያ ጥያቄዎቹን በክፍል ስራ በመስጠት በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎችን በእየግላቸው እየሰሩ መሆናቸውን በመዘዋወር ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ለተማሪዎቹ እንደየትምህርት አቀባበላቸው ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ሰርተው መጨረሳቸውን ካረጋገጡ በኋላ አስፈሊጊውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማሰራት ይችላሉ፡፡

- መልስ፡-

1. መ 2. መ 3. ሀ 4. ለ 5. መ 6. ለ

ተግባር ሁለት፡- ቃላት

ሀ. በዚህ ስር የቀረቡት ተተኳሪ ቃላት የተማሪዎቹን የቃላት እውቀት ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ ናቸው፡፡

- በተማሪ መፅሀፉ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ተተኳሪ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮቹን አሟልተው እንዱፅፉ ያግዟቸው፡፡
- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን በማስታወሻ ደብተራቸው በመገልበጥ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ቀጥሎም በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ተናጠላዊ ፍች ይንገሯቸው፡፡
- ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች አረፍተ ነገሮቹን አሟልተው እየፃፉ መሆናቸውን ይከተሏቸው፡፡
- እገዛ የሚያስፌልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ካሉ እንደየፍላጎታቸው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡
- ተገቢውን እርማት ይስጡ፡፡
- መልስ፡-

1. ማሰላሰል 2. ፈንጠዝያ 3 አመለካከት

4. በትጋት፣ ትርፋማ 5.ብድር

ለ. በዚህ ስር የተለያዩ ሀረጋት የቀረቡ ሲሆን ተመሳሳያቸውን በማጣመር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡

- በቅድሚያ በተማሪ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ምሳሌ ያሰሯቸው፡፡

ከዚያም ጥንድ ጥንድ በመሆን በጋራ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

- እየተዘዋወሩ በመመልከት ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በመስራት እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

- ጥንደ ጥንድ ሆነው ጥያቄዎችን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ በቡድን በመሆን እንዲተራረሙ ያድርጓቸው፡፡
- በመጨረሻም አስፊሊጊውን እርማት በመስጠት ትክክለኛውን መልስ እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡-

1. ሐ 2. ለ 3. ሠ 4. ሀ 5. መ

ተግባር ሶስት፡- መፃፍ

መምህር፡-

በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የፅህፈት ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ተማሪዎች ቀድመው የቤት ስራ በመስጠት‹‹ስንፍናንና በርትቶ መስራትን›› የተመለከቱ ተረቶችን አንብበው እንዲመጡ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን ሰርተው መምጣታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተግባራቱን የሚሰሩበትን መንገድ ያመቻቹ፡፡
- ከላይ ‹‹ሰነፍ ይከስራል የሰራ ይከብራል›› የሚለውን ምንባብ በድጋሚ እንዱያነቡት በማድረግ ዋናውን ሀሳብ በአራት አረፍተ ነገር ኣሳጥረው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈሊጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን በየተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ለሁለም ተማሪዎች እንደየትምህርት አቀባበላቸው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- የተሻለ ለሰሩ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጡ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢዎች፣ የቃላት ቻርት፣

**ክፍል ሶስት፡- ቃላት**

**ተግባር አንድ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ቃላት**

*መምህር፡-*

*ሀ. በቅድሚያ በተማሪዎቹ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡*

- *በቅድሚያ ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ይንገሯቸው፡፡*
- *የተማሪዎቹን ሙከራ ከተመለከቱ በኋላ ሌሎች ተጨማሪ መልሶችን ይስጧቸው፡፡*
- *ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛ ይደረግላቸው፡፡*

*መልስ፡-*

1. ለበሰ፣ ነከሰ፣ ገመሰ፣ ቦደሰ…
2. ሰበረ፣ ነከረ፣ ሰወረ፣ ገበረ…
3. ታረመ፣ ታመመ፣ አለመ…
4. አከለ፣ ወከለ፣ ከለለ…
5. ፈረደ፣ አረደ፣ ወረደ…
6. ከረፋ፣ አካፋ፣ አሰፋ… ወዘተ. የመሳሰሉትን ቃላትን እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡

*ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ቃላት ተስማሚያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡*

- *በዚህ ተግባር የቀረቡት ቃላት የሚዛመዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ተዛምዷቸው በተመሳሳይ ወይም በተቃራኒ ፍቺ ሳይሆን በቃላቱ ውህደት ምክንያት ነው፡፡*
  *ለምሳሌ- የእግር ሹራብ የሚለውን ስንመለከት የእግር እና ሹራብ ከሚለ ሁለት የተለያዩ ተጣማሪ ቃላት የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች እንዲህ አይነት ቃላትን እንዲያጣምሩ በመፅሀፋቸው ላይ ቀርቧል፡፡*

- በመጀመሪያ ምሳሌውን በመስራት እንዴት ቃላቱን እንደሚያጣምሩ ያሳይዋቸው፡፡
- ከዚያም ምሳሌውን መረዳታቸውን በልዩ ልዩ የምዘና ዘዴ ካረጋገጡ በኋላ በቤት ስራ ወይም በክፍል ስራ መልክ ስርተው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ከዚያም የሰሩትን የቤት ስራ ወይም የክፍል ስራ በማረም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ ተነስተውም ተጨማሪ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አይርሱ፡፡

መልስ፡-

1. ለ 2. መ 3. ሠ 4. ሀ 5. ረ 6. ሐ

ሐ. ይህ ተግባር የቀረበው ተማሪዎች ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ነው፡፡

- ተማሪዎቹ ቃላቱን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በማስፈር ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎችን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡

በመጨረሻም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

መልስ፡-

1. መካከለኛ 2. ግዴለሽ 3. ንትርክ፣ ጭቅጭቅ

4. ማወደስ፣ ማሞካሸት 5. ጨዋ 6. ሀብታም፣የሞላለት

7. አደፈጠ

ክፍል አምስት፡- ፅህፈት

ተግባር አንድ፡- መፃፍ

- በዚህ ተግባር ስር የቀረበው ተማሪዎች በሳምንት ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባር በጽሑፍ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ነው፡፡

አተገባበሩም

- ቀደም ብለው የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም ሁለም ተማሪዎች በሳምንት ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባር በጽሑፍ በማስፈር በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች የወደፉት ራዕያቸውን በእቅድ መላክ አዘጋጅተው በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- አላማቸውን ወይም ራዕያቸውን ከግብ ለማድረስ ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑም እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ተግባር አንድ፡- አያያዦች

መምህር፡- ሀ. በዚህ ተግባር ስር አያያዦችን መለየት እንዲሁም መጠቀምን የሚያስችሉ ተግባራት ቀርበዋል፡፡

- በቅድሚያ ካሁን በፊት ስለአያያዦች የቀረበውን ማስታወሻ በቃል ያስታውሷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- መስራታቸውንም እየተዘዋወሩ ክትትል በማድረግ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ይስጡ፡፡
- በመጨረሻም አስፈሊጊውን ግብረ መልስ በመስጠት ትክክለኛውን የአያያዦች አጠቃቀም እንዲያውቁ ያድርጓቸው፡፡

መልስ፡-

1. ነገር ግን 2. ወይስ 3. እንግዲህ 4. ምክንያቱም

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄችን በአግባቡ መስራታቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- አረፍተ ነገሮችን ሲመሰርቱ ተገቢነታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈሊጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- ከተማሪዎቹ ምላሽ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

ተግባር ሁለት፡- ቅጥያዎች

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ስር ቅጥያዎችን የተመለከቱ ተግባራት ቀርበዋል፡፡

- በቅድሚያ ስለቅጥያዎች ተገቢውን ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም ምሳሌዎችን ካሰሯቸው በኋላ በራሳቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች እንዲለዩ

ያድርጓቸው፡፡

- በቅድሚያ ምሳሌዎችን በማሰራት ፍንጭ ይስጧቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- አጫጭር ምንባቦች፣ ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ፣ የቃላት ቻርት፣ ሻሽ ቦርድ የሰዋስው ማጠራቀሚያ

*ማጠቃለያ*

*በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ስራን የተመለከቱ ምንባቦች አዳምጠዋል ፤አንብበዋል፡፡ ባዳመጡት ጽሑፍ መነሻነት በቃልና በጽሑፍ የሚመለሱ ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ እንዲሁም ‹‹ሰነፍ ይከስራል የሰራ ይከብራል›› የሚለውን ተረት አንብበው የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በጽሑፍ ገልፀዋል፡፡ ወደፊት ሊሰሩ ያሰቡትን ጉዳዮች በእቅድ አስፍረዋል፡፡ ለተለያዩ አዳዲስ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ አያያዦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መስርተዋል፡፡ ቅጥያዎችን ከቃላት ጋር አጣምረዋል፤ ከቃላት ነጥለው አመልክተዋል፡፡*

*ከዚህ በተጨማሪም የምዕራፉን ዋና ዋና ይዘቶች መሰረት በማድረግ የቀረቡትን የተለያዩ የክለሳ ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡*

*መምህር የምዕራፉን ዋና ዋና ዓላማዎች ከግብ ማድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚከተለትን ነጥቦች ትኩረት ውስጥ በማስገባት መገምገም ይችላሉ፡፡*

- *የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው በቃላቸው እንዲናገሩ በማድረግ፣*
- *የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በራሳቸው አገላለፅ አብራርተው መፃፋቸውን በመለየት*
- *የወደፊት እቅዳቸውን መፃፋቸውን በማየት*
- *ለቀረቡላቸው አዳዲስ ቃላት ፍች መስጠታቸውን በማየት*
- *አያያዦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረታቸውን በማረጋገጥ ግምገማዎችን ያከናውኑ፡፡*

## ምዕራፍ ዘጠኝ (15 ክፍለ ጊዜ)

### ባህል

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- አዳምጠው በምንባቡ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች ላይ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡
- ምንባብ አንብበው መልዕክቱን ይረዳሉ፡፡
- በተሰጣቸው ቃላት አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- አዳዲስ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡
- በአረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዶችን ይለያሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና
- መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

የአዲስ አመት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር፡-

- የማዳመጡን ተግባር ከማስጀመርዎ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማሰራት የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፤ የማዳመጥ ፍላጎታቸውንም ያነሳሱ፡፡
- አተገባበሩም በተቀመጡበት ወንበር ቡድን እንዱመሰርቱ በማድረግ በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፤
- ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ከሚያዳምጡት ምንባብ ጋር ግምታቸው ምን ያህል እንደተዛመደ ልብ እያለ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው፡፡
- ስዕሉን ተመልክተው የተገነዘቡትን ሀሳብ እንዲናገሩ በማድረግ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚከበሩ ትልልቅ በዓላትን እንዲዘረዝሩ ይንገሯቸው፡፡ ከህይወት ልምዳቸው ተነስተው የሚያከብሯቸውን በዓላት አከባበር እንዱናገሩ ያድርጓቸው፡፡ (ለምሳሌ፡- እንቁጣጣሽ፣መውሊድ፣ኢሬቻ፣ አሸንዳ…)
- የሚደመጠውን ምንባብ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በጽሑፍ እንዲደርሳቸው ያድርጉ፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩን በሚከውኑበት ሰዓት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምንባብ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ለእለቱ የተዘጋጀውን የማዳመጥ ምንባብ ለሁለት ጊዜ እንደሚነበብላቸው በመንገር ያንብቡላቸው፡፡ የሚደመጠውን ምንባብ በመቅረፀ ድምፅ ቀደም ብሎ ቀርፆ በማዘጋጀት ማስደመጥ ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የሚደመጠውን ምንባብ በአግባቡ እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥና በቀጣይ የሚመጣውን የማዳመጥ ክፍል በንቃት እንዲያዳምጡ የጊዜ መዳመጥ ጥያቄውን ያሰሯቸው፡፡

## የአዲስ አመት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ምንጭ እንደመሆኗ የተለያዩ የስልጣኔ አሻራዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገሩባት የኖረች፤ ወደፊትም በዚህ ትውልድ ቅብብሎሽ የምትኖር የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት አገር ናት፡፡ የዘመን አቆጣጠሩም በየአመቱ ከሚመጣው እንቁጣጣሽ በዓል ጋር ይያያዛል፡፡ በዚህም መሰረት ስለዘመን መለወጫ በዓል እንቁጣጣሽ ምንነትና ከበአል ጋር ተያይዞ የባህሉን ትልቅነት መቃኘት አስፈሊጊ ይሆናል፡፡ በየዓመቱ የእንቁጣጣሽ በዓል ማክበራችን የእንቁጣጣሽ ግብር የእንቁጣጣሽ ገፀ በረከት ብለን የምስራቹን ቃል ማሰማታችን ነው፡፡ እውነተኛው እንቁጣጣሽ የሚለው ቃል ‹‹ግጫ›› ነው በመሆኑም ልዩ ልዩ አበባዎች ተቀጥፈው የሚታሰሩበትና በአጠቃሊይ የሚጠሩበት ነው ብለው የሚተርኩም አሉ፡፡

አዱስ ዘመን ሲመጣ ምን ምን ነገሮችን ታደርጋላችሁ ?

በአዱስ ዓመት መጀመሪያ ቀን ልጆች ለወላጆች ለዘመድና ለጎረቤት አደይ አበባ የአዱስ ዓመት የበጎ ምኞት መግለጫ ስጦታ አድርገው ይሰጡ ነበር፡፡ እንግጫ ( የዘመን መለወጫ ጊዜ ልጃገረዶች ከአበባ ጋር እየጎነጎኑ የመልካም ምኞት ስጦታ የሚያደርጉት የሳር አይነት ነው፡፡ የመስከረም ወር ዝናብ የሚቆምበት፤ ፀሃይ የምትወጣበት ፣ ወንዞች ንፁህና ኩልል ያለ ውሃ የሚያወርድበት ፣አዝዕርቶች ማሸት የሚጀምሩበት፣ሜዳዎች ተራራዎችና ሸለቆዎች በአበቦች የሚያሸበርቁበትና የሚንቆጠቆጡበት ጥጆችና ህፃናት የሚፈነድቁበት፣የጨለማ የጭጋግና ደመናማ ሰማይ የሚገፈፍበት፤ ብርሃናማ ሰማይ የሚታይበት፤ የጨለማና የችግር ጊዜ የሚያበቃበት፣የደስታ የእሸት የፍሬና የጥጋብ ጊዜ የሚጀምርበት ፣ የወራቶች ሁሉ አውራ በሆነው መስከረም ወር በገባ የመጀመሪያው ቀን እንቁጣጣሽ ተብሎ የሚከበር ታላቅ በዓል ነው- ዘመን መለወጫ፡፡

በጥንት ጊዜ ዒፍ መሰቀል ‹‹የመስቀል ወፍ ›› የምትባለዋ ዒፍ እንቁጣጣሽ ‹‹የእንቁጣጣሽ ወፍ››ትባል ነበር፡፡ይህች ወፍ በልዩ ልዩ ህብረ ቀለሞች ተንቆጥቁጦና አሸብርቃ ለተፈጥሮ ውበት ከምትሰጠው ድምቀት በተጨማሪ ለብዙ ወራት ከጠፋችበት መጥታ ለሚያዩት ሁለ ደስታ የምትሰጥበት ወር ከወሩም የመጀመሪያው መስከረም 1 ቀን ታላቅ ርዕስ ዓውደ ዓመት ተብሎ መከበሩ አትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ ታላቅ የምስራች የሚሰማበት ዕለት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

አዱስ አባባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ቅፅ 7 ፣ቁ 12 መስከረም 2008 ላይ የተወሰደ፣ ባህል ወ ቱሪዝም

ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

ሀ. የዚህ ተግባር ዋና አላማ የተማሪዎችን የአዳምጦ መናገር ክሂልን ለመለየት የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ ጥያቄዎች ተካተውበታል፡፡

- በቅድመ ማዳመጥ የገመቱት ሃሳብና ያዳመጡት ምንባብ ምን ያህል ተዛምዶ እንዳለው በመጠየቅ እንዱናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- በቅድሚያ ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ ያገኙትን ዋና ዋና ሀሳብ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- በመቀጠል ቡድን ሆነው ያነሳቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች ከየቡድኑ አንድ አንድ ተወካይ እየተነሳ እንዱያቀርብ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎቹ ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ አዲዲስ ሊሆኑባቸው የሚችሉ ቃላትን ለቅመው በማውጣት በሰሌዳው ላይ ይፃፍላቸው፣በቅድሚያ ራሳቸው ተማሪዎቹ የቃላቱን ፍች እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ በመጨረሻም የቃላቱን ትክክለኛ ፍች ያስቀምጡላቸው፡፡
- የእንቁጣጣሽ በዓል በሚከበርባት ወቅት የሚሰጡ ስጦታዎችና መገለጫነታቸው ለምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስለሀገራችን የዘመን አቆጣጠር የሚያውቁት ነገር እንዳለ በመጠየቅ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ስለ መስቀል ወፍ በመጠየቅ የሚያውቁት ከሆነ እንዲያወሩ ያበረታቷቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዱያቀርቡ ያድርጓቸውና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎችን እንደየትምህርት አቀባበላቸው በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች መሳተፋቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተሻለ ተሳትፍ ለሚያደርጉ ተማሪዎች እውቅና ይስጡ፤ብዙም ተሳትፍ የማያደርጉትን ደግሞ ያበረታቷቸው፡፡

- የእለቱን ተግባር አስመልክቶ አጠቃላይ ግብረ መልስ ይስጡ፤ከግብረ መልሱም ተነስተው አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ሀሰት በማለት በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- እጅ እያወጡ የማይሳተፉ ተማሪዎችን ስማቸውን እየጠሩ እንዲመልሱ በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲሰጡ ያግዟቸው፤ ለምላሾቻቸውም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- በአጠቃላይ ለዚሁ ተግባር የሚሆን ግብረ መልስ በመስጠት የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

  መልስ፡-

1. እውነት 2. ሀሰት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. ሀሰት

ተግባር ሁለት፡- መናገር

መምህር፡-

- ይህ ተግባር የሚከናወነው የተማሪዎችን የንግግር ክህሎት ለማዳበር ነው፡፡
- አተገባበሩም በቅድሚያ ከአምስት እስከ ሰባት የሚሆኑ ተማሪዎችን የያዘ ቡድን ያደራጇቸው፡፡
- ከዚያም ባደራጁት ቡድን መሰረት በእንቁጣጣሽ ወቅት የሚዜሙ ወይም የሚባሉ ጨዋታዎችን አጥንተው እንዲመጡ ቀድመው ይስጧቸው ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች በየቡድናቸው እንዲሳተፉ ይንገሯቸው፡፡
- በመጨረሻም ያጠኑትን ጨዋታ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተግባሩን የተሻለ ለከወኑ ተማሪዎች ማበረታቻ ይስጡ፡፡
- አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ተማሪዎች ሌሎች ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ተግባራት መስጠት ይችላሉ፡፡

ተግባር ሶስት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች የተመሳሳይ ቃላት እውቀት ለማሳደግ ነው፡፡

ተማሪዎች በ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ ‹‹ለ›› ስር ተመሳሳያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያርጓቸው፡፡

- አተገባበሩም የክፍል ስራ በመስጠት ፍቻቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እየሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የተለየ ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎች ሰርተው እንደጨረሱ አስፈሊጊውን እርማት ይስጡ፡፡ ተገቢ ነው ያሉትንም ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳትም ሌሎች ቃላትን የተመለከቱ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

  መልስ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ሐ | 2. ረ | 3. መ | 4. ሠ |
| 5. ሰ | 6. ሀ | 7. ሸ | 8.ለ |

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት የተማሪዎችን የተቃራኒ ቃላት እውቀት ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- አተገባበሩም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ካሰፈሯቸው በኋላ በፍች ተቃራኒ የሆኑትን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎችን መስራታቸውን ክትትል በማድረግ ያረጋግጡ፡፡
- በመቀጠልም ትክክለኛውን መልስ መስጠታቸውን ማስታወሻ ደብተራቸውን በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛዎት አይለያቸው፡፡
- ተጨማሪ ተግባራት ያስፈልጋል ብለው ካመኑ መስጠት ይችላሉ፡

መልስ፡-

1. ሐ 2. ለ 3. ረ 4. ሀ 5. መ 6. ሠ

ተግባር አራት፡- መፃፍ

መምህር፡- የዚህ ተግባር ዋና አላማ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ለማሳደግ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ ጥያቄዎች ተካተውበታል፡፡

- ቀደም ብለው ለተማሪዎች በዓል ሲመጣ የሚዘጋጁ ምግቦችን ፅፈው እንዲያመጡ ይዘዟቸው፡፡
- ከዚያም ፅፈው ያመጡትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ በማድረግ ይገምግሙ፡፡
- በመቀጠል ግምገማውን መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡ ሌላው በዓመት በዓል ወቅት የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳትን በዝርዝር ፅፈው እንዲመጡ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በአካባቢያቸው በድምቀት የሚከበርን አንድ ክብረ በዓል አከባበር ሂደትን መዝግበው በመምጣት ክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ይህም መረጃዎችን በመጠየቅ ፅፈው መምጣትን እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎችን መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡
- እገዛ ለሚሹና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ለተማሪዎች እንደዬትምህርት አቀባበላቸው የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ የተሻለ የፃፉ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፤ የሌሎች ደግሞ ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዱ እድል ይፍጠሩላቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ቅንጫቢ ፅሁፎች፣ የቃላት ቻርት…

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ባህል

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

*መምህር፡-*

- ይህ ተግባር የተዘጋጀው የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት ከፍ ለማድረግና ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት በውስጡ የሰፈሩ ሀሳቦችን እንዲገምቱ በማድረግ መነሳሳትን ለመፍጠር ነው፡፡
- ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ስዕሉን ተመልክተው የተረዱትን ሀሳብ እንዲናገሩ እድል ይፍጠሩላቸው፡፡
- ስለባህል ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ነገር እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የሰርግ ስነ ስርዓት እንዴት እንደሚከናወን ይጠይቋቸውና መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- ትንሽ አባላት ያለት ቡድን በማደራጀት እርስ በእርስ ለአምስት ደቂቃ ተነጋግረው ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ምንባቡን በመቅረፀ ድምፅ በማዘጋጀት እንዲያዳምጡት ያመቻቹላቸው፡፡
- ምንባቡን በሚያነቡበት ወቅት የንባብ ጊዜ ጥያቄውን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

### ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

*መምህር፡-*

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለመለየት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ዋና ሀሳብ እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡
- ከራሳቸው ህይወት ጋር እያዛመዱ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

- የባህል መግለጫ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ኢትዮጵያ ብዙ ባህል ያላት ሀገር እንድትሆን ያስቻላት ምክንያት ምን እንደሆነ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ለአይነ ስውራን ተማሪዎች ጥያቄዎች እያነበቡላቸው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ ምላሻቸውን ይቀበሉና አስፈሊጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ለሎች ባህል ነክ የሆኑ ተግባራቶችን በመዘርዘር ፅፈው እንዲመጡ በማድረግም ማበረታታት ይችላሉ፡፡

  ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡
- ተግባሩን የክፍል ስራ በመስጠት ያሰሯቸው፡፡
- ከዚያም ሁለም ተማሪዎች በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተዘዋውረው የተማሪዎችን ስራ በማየት ያግዟቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ክትትል ይደረግላቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች መልሳቸውን በቃላቸው እንዱሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

መልስ፡-

1. እውነት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. ሀሰት

ተግባር ሁለት፡- ቃላት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎች ለተመሳሳይ ቃላት ፍች እንዱሰጡ የቀረቡ ቃላት ናቸው፤ በዚህም የቃላት ፍች አቅማቸውን ለማዳበር ያግዛሉ።

- በቅድሚያ ይህን ተግባር እንዳመችነቱ በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ ማሰራት ይችላሉ።
- ለቃላቱ ሁለም ተማሪዎች ትክክለኛውን ፍች መስጠታቸውን ይከታተሉ።
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ለሁሉም ተማሪዎች አስፌሊጊው እገዛ ይደረግላቸው።
- ተማሪዎች መልሶቻቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው። መልስ፡-

1. ባላንጣ፣ ጠላት 2. ልምድ፣ ወግ 3. መገለጫ

4. ውበት፣ ድምቀት 5. ማጌጫ 6. ማስማማት፣ ሰላም ማውረድ

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት የተማሪዎችን የተቃራኒ ፍች እውቀት ለማሻሻል የሚያግዙ ናቸው።

- በቅድሚያ ይህን ተግባር እንዳመችነቱ በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ መስጠት ይችላሉ።
- ለቃላቱ ሁለም ተማሪዎች ትክክለኛውን ተቃራኒ ፍች መስጠታቸውን በመከታተል ድጋፍ ያድርጉላቸው።
- ተማሪዎች መልሶቻቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው።
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። እንደየትምህርት አቀባበላቸው ለሁሉም ተማሪዎች አስፌላጊው እገዛ ይደረግላቸው።

- መልስ፡-

1. ሞት 2. መነጣጠል፣ መለያየት 3.ብቸኝነት፣ ባይተዋርነት

4. ደስታ፣ ተድላ 5. መስቀል፣ ማውጣት

ሐ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት የተማሪዎችን አረፍተ ነገር የማዋቀር ችሎታ ለማሻሻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎቹ አረፍተ ነገር በሚመሰርቱበት ጊዜ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ክትትል ያድርጉ፡፡
- እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ግብረ መልስ በመስጠት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

ተግባር ሶስት፡- መፃፍ

መምህር፡-

- በዚህ ተግባር ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች የቤት ስራ በመስጠት ያሰሯቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን ሰርተው መምጣታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፌሊጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- አጫጭር ምንባቦች፣ የቃላት ቻርት..

ክፌል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ቃላት ተማሪዎች ቃላቱ አንድና ከዚያ ባሊይ ፍች ያላቸው መሆናቸውን እንዲያውቁ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም ለእያንዳንዱ ቃል ሶስት ሶስት ተመሳሳይ ፍች እንደሰጡ ያድርጉ፡፡
- ተገቢውን እርማት በመስጠት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማሰራት ይችላሉ፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍዎት አይለያቸው፡፡

መልስ፡-

1. አደብ ገዛ = ተረጋጋ፣ ረገብ አለ፣ ሰከነ
2. መመንጠር = ማፅዳት፣ ማጥራት፣ ማስወገድ
3. እንከን = ጉድለት፣ ስህተት፣ ስሃ
4. አጠናቀቀ = አበቃ፣ ጨረሰ፣ አከተመ
5. ተገነዘበ = ተረዳ፣ አስተዋይ፣ አወቀ

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሻሻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በቅድሚያ ይህን ተግባር እንዳመችነቱ በክፍል ስራ ወይም በቤት ስራ መልክ መስጠት ይችላሉ፡፡
- ለቃሊቱ ሁለም ተማሪዎች ትክክለኛውን ተቃራኒ ፍች መስጠታቸውን በመከታተል ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎች መልሶቻቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተገቢውን ግበረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ለሁሉም ተማሪዎች አስፊሊጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ሻሸ ቦርድ፣ የቃላት ቻርት…

ክፍል አራት፡- ፅህፈት

ተግባር አንድ፡-

መምህር፡-

ይህ ክፍል የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማሻሻል የተዘጋጀ ነው፡፡

- ተማሪዎች በመፅሀፋቸው ሊይ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት በስርዓት በማዋቀር አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- አረፍተ ነገሮችን በሚያዋቅሩበት ጊዜ ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ መጠቀማቸውን ይከታተሉ፡፡
- እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- መልሳቸውን ተራ በተራ እየተነሱ እንዲናገሩ ያደፋፍሯቸው፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
  ልዩ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች ደጋፍዎት አይለያቸው፡፡
  ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

ተግባር አንድ፡- መስተዋድድ

መምህር፡-

- በተማሪዎች መፅሀፍ ሊይ ስለመስተዋድድ የቀረበውን ማስታወሻ ያስረዷቸው፡፡
- ልዩ ልዩ ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት ፅንሰ ሀሳቡን የበለጠ እንዲረዱ ያብራሩላቸው፡፡
- ከዛም በዚሁ ክፍል ስር የቀረቡትን ተግባራት ያሰሯቸው፡፡
  ሀ. በዚህ ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ከስሞች ላይ መስተዋድዶችን ለይተው እንዲያወጡ ያግዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

- ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡
  ለ. በተማሪ መፅሀፍ ሊይ በሰንጠረዡ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት መካከል መስተዋድድ የሆኑትን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ተግባራቱን እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታን ይፍጠሩላቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈሊጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ ከግብረ መልሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡
  ሐ. በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መስተዋድዳዊ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይስጧቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ጥሩ ተሳትፍ ያላቸውን ተማሪዎች ያበረታቱ፤ ደከም ላሉት ደግሞ ተጨማሪ የመለማመጃ ተግባራትን እንዲሰሩ በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊው እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ‹‹ባህል›› የሚሉ ርዕስ ተነስቷል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተማረዎች ስለእንቁጣጣሽ በዓል የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው የተረዱትን በቃል ተርከዋል፡፡ እንዱሁም ስለባህልና መገለጫዎቹ በማንበብ የተረዱትን ዋና ሃሳብ በራሳችው አገላለፅ አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም የአዳምጦና የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተለያየ መንገድ ሰርተዋል፡፡ የተለያዩ ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገር መስርተዋል፡፡ ከአንድ በላይ ፍች ላላቸው ቃላት ትርጉም ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ስለመስተዋድደች አንስተዋል፡፡ መስተዋድዶችን ከቃላት ውስጥ ለይተው አመልክተዋል፤ መስተዋድዶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መስርተዋል፡፡ የምዕራፉን ዋና ዋና ይዘቶች ታሳቢ በማድረግ ለቀረቡት የክለሳ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

መምህር የምዕራፉ አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በሚከተለው መልኩ መገምገም ይቻላል፡፡

- ያዳመጡትን ምንባብ ተረድተው መልዕክቱን መናገራቸውን በመገምገም፤
- ያነበቡትን ምንባብ ዋናውን ሀሳብ ለይተው ማብራራታቸውን በማረጋገጥ፤
- የቀረቡላቸውን ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረታቸውን በማየት፤
- ለአዳዲስ ቃላት ፍች መስጠታቸውን በመለየት፣
- ከአረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዶችን መለየታቸውን በማረጋገጥ ግምገማዎትን ማከናወን ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ አስር (15 ክፍለ ጊዜ)

## ገበያ

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

ቅድስትና የገበያ ውሎዋ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡
- በክፍል ደረጃቸው ያነበቡትን ጽሑፍ ዋና ሀሳብ ያብራራሉ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡
- አያያዥ ቃል በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገር ይፅፋሉ፡፡

የምዕራፍ ይዘቶች፡-

- ማዳመጥና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መፃፍ
- ሰዋስው

መምህር፡-

- በዚህ ስር የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት ለማነሳሳትና የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ የተዘጋጁ ናቸው፡፡
- በመጀመሪያ ስዕሉን ተመልክተው የተረዱትን ሀሳብ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠሉም ተማሪዎቹ ከወላጆቻቸው ጋር ገበያ ሄደው ያውቁ እንደሆነ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡
- በመጨረሻም ገበያ ውስጥ ምን ምን ነገሮችን እንደተመለከቱ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን በዝርዝር እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ምንባቡን ቀድመው በጽሑፍ እንዲያገኙ እድሉን ይፍጠሩላቸው፡፡
- የማዳመጥ ተግባሩ በሚከናወንበት ሰዓት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችም የተሰጣቸውን ምንባብ እንዲያነቡት ያርጓቸው፡፡
- የሚደመጠውን ምንባብ ሁለት ጊዜ እንደሚነበብላቸው በመንገር ዝግጁ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎቹ እያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም የሚቀጥለውን የምንባብ ክፍል በትኩረት እንዲያዳምጡ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄውን ይጠይቋቸውና መልሳቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

ቅድስትና የገበያ ውሎዋ

ከእለታት አንድ ቀን የእነቅድስት አማርኛ መምህር ስለባህላዊ ግብይት ስርዓት ዘገባ ፅፋችሁ እንድትመጡ ሲል አዘዟቸው፡፡ ቅድስትም ለእናትና አባቷ ገበያ ሄዳ ዘገባ መፃፍ እንዳለባት ነግራቸው ወደ ቅዳሜ ገበያ አብራቸው ሄደች፡፡ ቅድስት በመንገድ ላይ ያየችውን ነገር ሁሉ አንድ ጊዜ እናትዋን ሌላ ጊዜ ደግሞ አባቷን እየጠየቀች እነሱም እየመለሱላት ከገበያ ቦታው ደረሱ፡፡

የገበያ ቦታው ከከተማው ትንሽ ወጣ ብሎ ያለ ሰፊ ሜዳ ሲሆን በላስቲክ የተወጠሩ የሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫዎች በብዛት ይታዩበታል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ በድንጋይ ካብ የተካቡ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦች የሚቀመጡባቸው ድርድሮችም ይታያሉ፡፡

ቅድስት እነዚህን ነገሮች ሁሉ ተዘዋውራ እየተመለከተች በማስታወሻዋ ላይ ትፅፋለች፡፡

ወላጆቿም የግብይት ስርዓቱን በሚገባ ያስረዷታል፡፡ እሷም ያልገባትንና መፃፍ የምትፈልገውን  እንዲያብራሩላት ትጠይቃለች፡፡ ወላጆቿም ጥያቄዋን ለመመለስ በፍፁም አይሰለቹም፡፡ በዚሁም ሁኔታ ከአንደ ተራ ወደ ሌላ የገበያ ተራ በመንቀሳቀስ ቅኝት አደረጉ፡፡ እነቅድስት በሄዱበት ሁሉ ሸማችና ገዥዎች በዋጋ ሲከራከሩ አስተውለዋል፡፡ የባህላዊ ግብይት ስርዓቱንም ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ በአትኩሮት መመልከታቸውን ቀጠሉ፡፡

ቅድስት የመዘገበችውን ማስታወሻ በቀጣይ ምን የምታደርግ ይመስላችኋል ?

በዚህ ዓይነት ብዙ የገበያ ድርድሮችን ሲመለከቱ፣ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ደግሞ ሲገዙ ዋሉ፡፡ ከዚያም ሲጨርሱ ወደ ቤታቸው ጉዞ ጀመሩ፡፡ እቤት እንደደረሱም ቅድስት ትንሽ እረፍት ካደረገች በኋላ ወደ ጥናት ክፍሉ ገባች፡፡ የያዘችውን ማስታወሻ እያገለበጠች በጥሞና ካነበበች በኋላ የገበያ ውል ዘገባዋን እንደገና አደራጅታ ፃፈች፡፡ ቅድስት ሰኞ እለት በጠዋት ተነስታ ቁርሷን በልታ ተዘጋጅታ ስትጨርስ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡ ወደ ክፍሉ እንደገባችም የአማርኛ መምህራቸው ወዲያው ተከትለው ገቡ፡፡መምህራቸውም የቤት ስራ መስጠታቸውን አስታውሰው ዘገባውን እንዲያነቡ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡ ቅድስት በፍጥነት እጇን አወጣችና ሲፈቀድላት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ዘገባዋን አነበበች፡፡መምህሯና ጓደኞቿ በተመስጦ ሲያዳምጡ ቆይተው ስትጨርስ የአድናቆት መግለጫቸውን በጭብጨባ አሰሙ፡፡

ምንጭ፡ - ት / ሚ እና በአማራ ብ / ክ / መ / ት / ቢሮ በትብብር ካዘጋጁት ለማስተማሪያነት ተሸሽሎ ተወሰደ

ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ክሂል ለመረዳት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ተማሪዎች ከዳመጡት ምንባብ ውስጥ የማያውቋቸው አዳዲስ ቃላት ካሉ ለይተው በማውጣት በክፍል ጓደኞቻቸው በጥያቄ መልክ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን በቡድን በቡድን በመሆን እንዲነጋገሩበት ያድርጓቸው፡፡
- በቡድን ተወካይ አማካኝነት የደረሱበትን ዋና ዋና ሀሳብ እንዲናገሩ ያድርጓቸው
- ባህላዊ የግብይት ስርዓት ምንነትን ይጠይቋቸው፤ መልሶቻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡
- የመማር ማስተማሩ ሂደት ሁለንም ተማሪዎች ያሳተፈ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

- እንደየትምህርት አቀባበላቸው የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ይጠቀሙ፡፡(ለምሳሌ፡- ተማሪዎች በማየት፣ በመስማት፣ በመዳሰስ፣ …) ለሚማሩ ተማሪዎች እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸውና አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም ለተግባሩ አጠቃላይ ግብረ መልስን ይስጧቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙትም ሌሎች ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ከአዳመጡት ምንባብ በመነሳት የንግግር ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያስችሉ ናቸው ተብለው የቀረቡ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹም የቀረቡት ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት እንዲመልሱ በማድረግ ለእያንደንዱ ጥያቄ ምክንያቱን እንዲናገሩ ያበረታቱዋቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፍ ማድረጋቸውን ያረጋግጡ፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሶቻቸውን ከነምክንያቱ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያደፋፍሯቸው፡፡
- ለተማሪዎቹ እንደየትምህርት አቀባበላቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን ተራ በተራ ከተናገሩ በኋላ አስፈላጊውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- እንደየ ሁኔታው ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትንም በመስጠት የእለቱን ትምህርት ማጠናከር ይችላሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- መናገር

መምህር፡-

- ይህ ተግባር የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የተዘጋጀ ነው፡፡አተገባበሩም ነቢያት ሻጭ ነጋዴ ሆና ፣ይልቃል ደግሞ ገዥ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በሁለቱ መካከል የተደረገውን ምልልስ መነሻ በማድረግ እናንተም ጭውውት አድርጉ በማለት ቀድም ብለው ይዘዟቸው፡፡

- በመቀጠልም ጭውውቱን ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመናገር ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዟቸው፡፡
- ጭውውታቸውን በማዳመጥ ጥንካሬያቸውን ያበረታቱ፤መሻሻል ያለበትን ይጠቁሙ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ክፍል ውስጥ ያቀረቡትን ጭውውት በማየት ግበረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱ ተነስተው ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማለማመድ ይችላሉ፡፡

ተግባር ሶስት፡- ቃላት

ሀ. በዚህ ስር የቀረቡት ተግባራት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲፅፉ በማድረግ የክፍል ስራ ይስጧቸው፤ ከዚያም ለቃላቱ ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡
- የክፍል ስራ በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ክፍል ውስጥ በመዘዋወር ይከታተሏቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው አሳታፊ የሆነ ተግባር ይስጧቸው፡፡
- ደብተራቸውን በማረም ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ከግብረመልሱ በመነሳት ተጨማሪ ልምምድ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡

መልስ፡-

1.ሙገሳ 2.ምልከታ 3.በጥሞና 4.ሪፖርት 5.መግዛትና መሸጥ

- ለሚከተለት በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለቀረቡት ሀረጋት ተስማሚያቸውን ከ ‹‹ለ›› ረድፍ ጋር እየመረጡ እንዲያዛምዱ ያግዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲሰሩ ክትትል ያድርጉላቸው፡፡
- የተሻለ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ያበረታቱ፤ የመይሳተፉትን ደግሞ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- የቀረቡትን ቃላት በትክክል ማዛመዳቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳትም ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

መልስ፡-

1. ለ 2. መ 3. ሀ 4. ሐ 5. ሠ

ተግባር አራት፡- መፃፍ

መምህር፡-

- ይህ ተግባር የተዘጋጀው የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል የቀረበ ነው፡፡
- አተገባበሩም ቀደም ብለው የቤት ስራ በመስጠት ይሆናል፡፡
- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ወደሚገኝ ገበያ ከወላጆቻቸው ጋር በመሄድ ባህላዊ የግብይት ስርዓቱ እንዴት እንደሚከናወን አይተው ፅፈው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡
- የፃፉትን ጽሑፍ ይገምግሙላቸውና ያበረታቷቸው፡፡
- ፅሁፈን በሚያዘጋጁበት ወቅት ከዚህ በፊት የተማሯቸውን ስርዓተ ነጥቦች በተገቢው ቦታ እንዲጠቀሙ ያስታውሷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን ሰርተው መምጣታቸውን ይከታተሉ፡፡

- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሰረት ያደረጉ ተግባራትን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዱ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎችም ተግባሩን በብሬል ፅፈው በመምጣት ክፍል ውስጥ እንዱያነቡ ያደፋፍሯቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ደግሞ ፅፈው እንዲመጡ በማድረግ ስራቸውን ይገምግሙላቸው፡፡
- ለሁሉም ተማሪዎች ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መሌሱ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት የመፃፍ ክሂላቸውን ማዳበር የሚችሉበትን እድል መፍጠር ይችላሉ፡፡

*መርጃ መሳሪያ፡- የድምፅ መቅጃ ቁሳቁሶች፣ ቅንጫቢ ፅሁፎች*

**ክፍል ሁለት፡- ንባብ**

**አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ**

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

*መምህር፡-*

- በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት ለማነሳሳት የተዘጋጁ ናቸው፡፡
- አተገባበሩም ተማሪዎች በተቀመጡበት ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲወያዩበት ያድርጓቸው፡፡
- ስዕሉን ተመልክተው የተረዱትን ሀሳብ እንዲናገሩ በማድረግ መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡ ፡
- ከርዕሱ ተነስተው የምንባቡን ሀሳብ እንዱገምቱ በመጠየቅ መልሳቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ምንባቡን በአትኩሮት እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- የምንባብ ሂደቱን በሚተገብሩበት ወቅት የጊዜ ንብብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- ያነበቡትን ይከታተሉ ፤ለውጣቸውንም ያበረታቷቸው፡፡

- ለዓይነ ስውራን ተማሪዎች ምንባቡን ቀድሞ በመቅረፀ ድምፅ በማዘጋጀት ይስጧቸው፡፡ ወይም ሌሎች ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማሻሻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በቡድን በቡድን በመሆን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ከየቡድኑ አንድ አንድ ተማሪ የተወያዩበትን ሃሳብ እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚታወቁ ዋና ዋና የገበያ ቦታዎችን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው፡፡
- ከዘረዘሯቸው የገበያ ቦታዎች ውስጥ በትልቅነቱ የሚታወቀው ማን እንደሆነ ይጠይቋቸውና መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡ ትልቅ ያስባለውን ምክንያትም እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ጥያቄዎቹ እየተነበቡላቸው መልሳቸውን በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

ለ. በዚህ ተግባር ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ሀሳብ እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት በቃል እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

- ሁለም ተማሪዎች ተሳትፍ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ለሁለም ተማሪዎች አመች የሆነ የማስተማር ዘዴን ይከተሉ፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡
- ከግብረ መልስ በመነሳት ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡

ተግባር ሁለት፡- መናገር

መምህር

- በዚህ ተግባር ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደግብአት ተጠቅመው ተማሪዎች የእርስ በርስ ንግግር እንዲያርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡
- ጠይቀው ያመጡትን መረጃ ከአካባቢያቸው ጋር በማስተሳሰር እንዲናገሩ ይፍቀዱላቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡ ሃሳባቸውን በንግግር በሚያቀርቡበት ጊዜ ድፍረት እንዲላበሱና በራስ መተማመንን እያጎለበቱ እንዲሄዱ ለመናገር ሰፊ እድል የሚሰጡ ተግባራትን በተጨማሪ ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግዎን ያስታውሱ
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡
- ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ከግብረ መልሱ ተነስተው ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት ያለማምዷቸው፡፡

ተግባር ሶስት፡- ቃላት

መምህር፡-

በዚህ ተግባር በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ስራ በመስጠት ሁሉም ተማሪዎች በማስተዋሻ ደብተራቸው እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ከዚያም የተማሪዎችን ምላሽ ደብተራቸውን በማረም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ሁለንም ተማሪዎች አሳታፊ ተግባር ይስጧቸው፡፡

ተግባር አራት፡- መፃፍ

ይህ ተግባር የተዘጋጀው የተማሪዎችን መፃፍ ክሂል ለማሻሻል ሲሆን በውስጡም ሶስት የተለያዩ ጥያቄዎች ተካተውበታል፡፡

- ወላጆቻቸውን ጠይቀው ፅፈው እንዲመጡ የተሰጣቸውን የቤት ስራ በትክክል ፅፈው መምጣታቸውን በማየት የተሻለ ለጻፉ ተማሪዎች የቃል ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡ይህም የተለያዩ መረጃዎችን በመጠየቅ በጽሑፍ የማቀናጀት ችሎታቸው እየዳበረ ስለሚመጣ ያበረታቷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ምላሻቸውን በቃል እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡
- እንደየትምህርት አቀባበላቸው ሁለንም ተማሪዎች አሳታፊ የሆነ ተግባር ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ቅንጫቢ ፅሁፎች፣ ተረቶች፣ አጫጭር ታሪክ

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር አንድ፡- ተቃራኒና ጥምር ቃላት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ስር የቀረቡት ቃላትን የተቃራኒ ፍች እውቀት ለማሻሻል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ይከታተሉ፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልሳቸውን እንዲናገሩ በማድረግ ከመልሳቸው በመነሳት ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

መልስ፡-

1.ተንቀረፈፈ 2.ተናጋሪ 3.ታናሽ 4.ተረጋጋ 5.አጣላ

ለ. በዚህ ተግባር ስር የተለያዩ ጥምር ቃላት ፍች በአዛምድ መልክ ቀርበዋል፡፡

- በመሆኑም ተማሪዎች በ ‹‹ሀ›› ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ከ ‹‹ለ›› ረድፍ ተመሳሳያቸውን በመፈለግ እንዲያዛምዱ ይንገሯቸው፡፡
- ይህን ተግባር የክፍል ስራ በመስጠት ተማሪዎች በመስታወሻ ደብተራቸው በማስፈር እንደያዛምዱ ይርዷቸው፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባሩን እየሰሩ መሆናቸውን በመዘዋወር ይመልከቱ፡፡
- በዚህ ወቅት እገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካለ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍዎት አይለያቸው፡፡
- በመጨረሻም የተማሪዎችን ደብተር በማረም ግብረ መልስ ይስጡ፤ ትክክለኛውን መልስ በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ሌሎች ተጨማሪ ተመሳሳይ ተግባራትን በመስጠት ማሰራት ይችላሉ፡፡

መልስ፡-

1. ሐ 2. ሀ 3. ሠ 4. መ 5. ለ

ሐ. ተማሪዎች በዚህ ስር የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፌተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ቃላቱን በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- በሚመሰርቱት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ከአሁን በፊት የተማሯቸውን ስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያስታውሷቸው፡፡
- የመሰረቱት አረፍተ ነገር ስርዓቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባራቱን መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ለሁለም ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው አስፈላጊውን የመማር ስልት ይከተሉ፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- የቃላት ቻርት፣ ፍላሽ ካርድ፣ የቃላት ሰንጠረዥ

ክፍል አራት፡- ፅህፈት

መምህር፡-

በዚህ ክፍል ስር የተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ማጎልበት የተዘጋጁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

- በመጀመሪያ ‹‹አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ›› የሚለውን ምንባብ ደግመው በማንበብ ዋናውን ሀሳብ እንዲያወጡ ይንገሯቸው፡፡
- ከዚያም ዋናውን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አሳጥራው እንዲፉ ይንገሯቸው፡፡
- የፃፉትን ማብራሪያ ይመልከቱላቸው፡፡
- በቡድን በመሆን በአካባቢያቸው የሚገኝ አንድ የሌብስ መሸጫ ሱቅ በመሄድ የዋጋ ዝርዝር ዘገባ በመፃፍ እንዱመጡ ይዘዟቸው፡፡ በፅሁፋቸው ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማቸውን ይመልከቱ፡፡
- ሁለም ተማሪዎች ተግባሩን መስራታቸውን ይከታተለ፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- አይነ ስውራን ተማሪዎች ፅፈው በመምጣት እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

ተግባር አንድ፡- አያያዞችን መለየት

መምህር፡-

ሀ. በዚህ ተግባር ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች አያያዦችን ለይተው በማስመር እንዲያመለክቱ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ይንገሯቸው፡፡
- ከዚያም አያያዥ ቃላቱን ለይተው እንዲያሰምሩበት ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት እና ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት ይችላሉ፡፡

በ ‹‹ለ›› እና ‹‹ሐ›› የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ካሁን በፊት የተማሯቸውን የቃል ክፍሎች እንዲያስታውሱ የሚያግዙ ናቸው፡፡

- ባለፈው ምዕራፍ ስለቃላት ክፍል የተማሩትን ያስታውሷቸው፡፡
- ከዚያም ሁለም ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ከግብረ መልሱ በመነሳት ለሎች ተጨማሪ ተግባራትን መስጠት

መ. በዚህ ተግባር ስር አያያዥ ቃላት ቀርበዋል፡፡

- እነዚህን አያያዥ ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ይንገሯቸው፡፡
- አረፌተ ነገሮቹን ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- አያያዥችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መስራታቸውን ይመልከቱ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መስራታቸውን ያረጋግጡ፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈሊጊው ድጋፍ ይደረግላቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ስርዓተ ነጥቦችን የያዘ ሰንጠረዥ፣ ሻሽ ቦርድ፣ ፍላሽ ካርዶች

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ገበያ የተመለከቱ ሁለት ምንባቦችን ተነበዋል፡፡ ተማሪዎች የመጀመሪያውን ምንባብ አዳምጠው የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን ሰርተዋል፡፡ አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ የሚለውን ምንባብ አንብበው የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡ የምንባቡን ፍሬ ሃሣብ በአንቀፅ ለይተው አብራርተው ፅፈዋል፡፡ ከምንባቡ ለወጡ አዲዱስ ቃላት ፍች ሰጥተዋል፡፡

ለተለያዩ ጥምር ቃላት ፍች ሠጥተዋል፡፡ የተለያዩ አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መስርተዋል፡፡ የምዕራፉን ዋና ዋና የትምህርት ይዘቶች መነሻ በማድረግ የቀረቡትን የክለሳ ጥቂያዎች ሰርተዋል፡፡

መምህር የምዕራፉ ዓላማ ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የግምገማ ስልቶች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- የተሰጣቸውን ምንባብ አዳምጠው የተረዱትን በቃል መናገራቸውን በመለየት፤
- የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው ዋና ሃሳቡን በራሳቸው አገላለፅ ማብራራታቸውን በማረጋገጥ፤
- ከምንበቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት ትክክለኛ ፍች መስጠታቸውን በመለየት፤
- አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገር መፃፋቸውን በመለያየት ግምገማ ማድረግ ይችላል፡፡

## ዋቢ ጽሑፍች

ቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ (1995) ስነ ቃል፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፡፡

በሊይነሽ የሻው እና ቢረሳው ታደሰ (2010) አማርኛ 3ኛና 4ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ባህል ወ ቱሪዝም (2008) አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ቅፅ 7፣ ቁጥር 12፣ 7-8፡፡

ባየ ይማም (2004) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ፕሪንተር፡፡

አላምረው ገብረ ማርያም (2002) አማርኛ መማርያ መፅሀፍ 1-4ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

አስምረት ብስራት (2013) የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ

አብርሃም እንደሻው (ዓ/ም ያልተጠቀሰ) ኢትዮጲስ ቁጥር 2

አዲስ ዘመን (2013) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፡፡ ከዌብሳይት ላይ የተወሰደ፡፡

ከበደ ሚካኤል (1999) ታሪክና ምሳሌ ፡፡1ኛ መፅሀፍ፣አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ውዳላት ገዳሙ (2010) ብድሯን ያልከፈለች ወፍ፡፡ አጠቃላይ አማርኛ አጋዥ ከ1-4ኛ ክፍል ኤች ኬ አሳታሚ

ፍዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ትምህርት ሚኒስቴር (2011) የትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት አደረጃጀትና አሰራር፡፡ ንቁ በርታ ማተሚያ ቤት፡፡

ዲንኤል ወርቁ (2011) የተማሩት እህትማማቾች፡፡አዲስ አበባ፣USAID- READ II

PROJECT.

ዲንኤሌ ወርቁ (2011) የዛፎች ጠላት ማን ነው፡፡ አዲስ አበባ፡፡ USAID- READ II

PROJECT.

USAID (2019) **የሀና ጊዜ አጠቃቀም፡፡** አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT.

USAID (2019) **የመጓጓዣ አይነቶች ፡፡** አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT.

USAID (2019) **የቅድስት ውል ዘገባ፡፡** አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT.